ESQUARE ADVERTIZING

# ቀንዲል

Amharic Digital Magazine

ቅፅ-1 ቁጥር-2

ወርሀዊ



"..በእውቀት የተገነባ
እና በስነምግባር
የታነፀ ወጣት ከሌለ
ሃገር አይኖርም ።...."

**ሰለሞን ለማ ( ሶልጂት )**
( ኢንተርናሽናል ሰርከስ አርቲስት )

**#አጃኢብ**
ከፈጣሪ በታች ያለ ፈጣሪ

**#ጤና ይስጥልኝ**
የ2030 የአለማችን 3ተኛ ገዳይ በሽታ

**#ድሮና ዘንድሮ**
አድዋና ወጣቱ

# ማውጫ





3-4፨ሀገሬ
ኢትዮጵያውያዊነት በምላስ የምትናገረው ብቻ ሳይሆን በሀሳብ የምትማረው ትምህርት ቤት ነው።
( በሀይሉ ወንድይፍራው )

5-6፨አብርሆት
የግል መለያ
( Personal Branding)
( በ ሀና ሀይሉ )

7-10፨የአውደብሩሀን ገፆች
ቆይታ ከ ሰለሞን ለማ ጋር

11፨ድሮና ዘንድሮ
አድዋና ወጣቱ
( በ ናሆም ሸዋንግዛው )

13፨አጃኢብ
ከፈጣሪ በታች ያለ ፈጣሪ
( በ ያብስራ ካሳ )

15፨ጤና ይስጥልኝ
የ 2030 የአለማችን 3ተኛው ገዳይ በሽታ
( በ ፍራኦል መስፍን )

17፨ስነ-ፈለክ
( በ ዞስ ካለስ )

20፨ቅምሻ
ተስፋ የቆረጥኩት በተስፋ መቁረጥ ላይ ነው!
( በ ኤርሚያስ ደጀኔ )

22፨ቴክኖሎጂ
( በ ያሬድ ለማ )

23፨እልፍ ገፆች
( በ ዮናስ ሀ/ማርቆስ )

# የአዘጋጇ መልዕክት




ሰላም!! ውድ የመፅሔታችን ተከታታዮች ሰላምታዬ ባችሁበት ይድረሳችሁ!! በዛሬው መልዕክቴ አሁን አሁን በስፋት እየተንሰራፋና ስር እየሰደደ የመጣውን የአደንዛዥ ዕፅ(አሽሽ)የሚመለከተው አካል ትኩረት እንዲሰጠው መጠየቅን ይመለከታል። አሽሽ(ማሬዋና) የኢትዮጵያን ልጆች አቅም፡ጉልበት፡ ራዕይ እየገደለ ያለ፡ የብዙ ወጣቶችን እናቶች በልጆቻቸው እንዲያለቅሱ እያደረገ ያለ አስከፊ መርዝ ነው። ማሬዋና፡ ዊድ፡ኩሽ በተለምዶ አሽሽ እያሉ በብዙ የዳቦ ስሞች አሞካሽተው እና አሳምረው የሚጠሩት በሳይንሳዊ መጠርያው ካናቢስ(cannabis) ተጠቃሚዎችን ለስነልቦና፡ማህበራዊ፡ ኢኮኖሚያዊና ለብዙ የጤና ቀውስ የሚዳርገው አደንዛዥ ንጥረ ነገር ትውልድን ውስጥ ውስጡን እየጨረሰ ያለ፡ ከ HIV ና ካንሰር ለይቼ የማላየው አስከፊ፡ የመንግስትን ትኩረት ሚያሻው የገዳይ በሽታ ባህሪ ያለው ዕፅ ነው። ወጣቶች ይሄን አደንዛዥ ዕፅ ከተጠቀሙ በኋላ በከፊል አዕምሮ ነገሮች የማብሰልሰል:የማስተዋልና ነገሮችን የማስታወስ አቅሙን እንዲያጣ አለፍ ሲልም በከፊል እራሱን እንዲስት የሚያደርግ የስነ ልቦና ቀውስ፡የአዕምሮ : የልብ፡የሳንባና የተለያዩ የጤና እክሎችን የሚያመጣ ተክል ነው። በተለይ በአብዛኛው የዚህ ዕፅ ተጠቃሚዎች የሁለተኛ ደረጃና የመሰናዶ ተማሪዎች እንዲሁም በግልና በመንግስት ዩኒቨርስቲና ኮሌጆች የሚማሩ ወጣቶች መሆናቸው ነገሩን አጅግ አስከፊ እና አሳሳቢ ያደርገዋል። ሌላው ነገሩን ይበልጥ አስከፊ የሚያደርገው አንዳንድ የህግ አስከባሪዎች ሰለ ዕፁ ያላቸው አነስተኛ እውቀት እና የተጠቃሚዎቹ ዕፁን ለማዘዋወር እና ለመጠቀም የሚጠቀሙት የረቀቁ ዘዴዎች የዚህን ዕፅ በተገቢው ሁኔታ ለመቆጣጠር እንደተቸገሩ ለመረዳት የምርምር ወረቀትን አያሻም። መንግስትና ወላጆች እነዚህን ወጣቶች ነገ ሀገር ተረካቢ ትውልዶች ይሆናሉ በማለት ብዙ ጊዜ፡ገንዘብና አስፈላጊ ነገሮችን ተሟልቶላቸው ሳለ ይህ በብዙ የዳቦ ስሞች የሚጠሩት የመርዝ ባህሪ ያለው ተክል ግን የወጣቶቹን በራስ የመተማመን ስሜት በመሸርሸር፡ ለራስ ያላቸውን ግምት አሳንሰው እንዲያዩ በማድረግ፡ ውጤታማ እንዳይሆኑ በሱስ አንቆና ቆልፎ ብዙዎችን "እሩቅ አላሚ ቅርብ አዳሪ" እያደረጋቸው ያለ ትልቅ መርዝ ነው። ሌላው ከስነልቦናዊና ማህበራዊ እክሉ ባለፈ ያለው ኢኮኖሚያዊ ጉዳቱ የትየለሌ ነው። ወጣቶች ይህን የማሳቅና የማዝናናት መልዕክት ያለው ውስጥ ውስጡን ግን እየገደለ ያለውን መርዝ ለመግዛት ከ20 እስከ 50 ብር በቀን እንደሚያወጡ መረጃዎች አሉኝ። ይህም በወጣቶቹ ኢኮኖሚ ላይ ትልቅ ተፅዕኖ አለው። ታድያ የኢትዮጵያን ልጆች እያሳሳቀና እያዝናና እያሳበደና መና እያስቀረ ያለውን ዕፅ መላ እንዲበጅለትና የሚመለከተው የመንግስት አካል በአንክሮ እንዲመለከተው ላሳስብ እወዳለሁ።
ስለሆነም መንገስት ይህን ተክል በንቃት ተከታትሎ ከምንጩ የዚህን ዕፅ ዝውውር እንዲገታና እንዲያስቆም አደራ እላለሁ። ሚዲያው ስለዚህ ዕፅ አስከፊነት ሰፋ ያለ መረጃ እንዲሰጥና ወጣቱ ስለ ዕፁ ያለውን እውቀትና መረዳት መጨመር ላይ እንዲሰሩ ልጠቁም እወዳለሁ። ወላጆችም ልጆቻቸውን በቅርበት እንዲከታተሉ፡ ውሏቸውን እንዲፈትሹና ከልጆቻቸው ጋር ግልፅ የሆነ ውይይቶችን በማድረግ ልጆቻቸውን በማዳመጥና በመረዳት ከዚህ የመርዝ ባህሪ ካለው ተክል እንዲታደጉ ላሳስብ እወዳለሁ።ወጣቱም ከዚህ ጊዜያዊ ደስታ ከሚሰጠው የኋላኋላ ግን ለከፋ የስነልቦዊ፡ ማህበራዊ፡ ኢኮኖሚያዊ ቀውስ የሚዳርገውና ለሚያስለቅሰው አስከፊ ተክል ፈፅሞ እንዳቆጠብና እንዲርቅ በትህትና እጠይቃለሁ።

#ሱስ_ከፍሎ_ማበድ_ነው!!

_______ሰላማችሁ ይብዛ!_______

#ኤርሚያስ ደጀኔ

ዋና-አዘጋጅ:- ኤርሚያስ ደጀኔ
✆0912178520
Email:-
ermiyasdejene@gmail.com
Telegram:- @Jeremy00

አዘጋጅ:- ሀና ሀይሉ
✆0935965345
Email:-
Hanahailu016@gmail.com
Telegram:- @HanaHailu

አርታኢ:- አወት ሀይለስላሴ
✆0920152581
E-mail:-
awoth12@gmail.com
Telegram:- @Awicha12

የመፅሔት ዲዛይን እና Editing:-
እስራኤል
✆0920019699
Email:- Esrumh1@gmail.com
Telegram:- @EsruMH



በሀይሉ ወንድይፍራው
( መባ ጥቁር ሰው )



# «…ኢትዮጲያዊነት ከምላስ አልፎ ልብ ላይ የተገነባ የተግባር ትምህርት ቤት ነው…»

ጎሳ ብሄራችን ቢያልፍ ከሰማኒያ
በተሰፋዋ ምድር በኢትዮጲያ
ሁሉም ካንድ እናት ነው ከአቢሲኒያ
ልዩነት አይፈጥርም ፍትህ መቸገሬ
ልዩነት አይፈጥርም መብት መቸገሬ
ልዩነት አይፈጥርም እውነት መቸገሬ
የአንድነት ምንጭ ናት እምዬ ሀገሬ።

የኔ ገና የሰው ልጅ የተፈጠረበት ነገር በቅጡ ሳይገባው ከአቢሲንያ ምድር የተገኙ የሰው ልጆች ለመላው አለም የእውቀት ብርሀን አሳዩ፤ በተለያየም ጊዜ ይህች የጠቢባን ምድር እልፍ ጠበብቶችን ለአለም አበረከተች ከታላቁ ፈላስፋ አጼ ዘርዓይቆብ እስከ ሜትር አርቲስት አፈወርቅ ተክሌ ለአለም ጽልመት ብርሀን የሆኑ ታላላቆችን በኪነ- ጥበብ፣ በስዕል፣በመሪነት ወ.ዘ.ተ ለአለም ያበረከተችው ውዷ ሀገራችን ኢትዮጲያ ይህን ታላቅነቷን በማይጠፋ ቀለም የጻፈችው ከሀሳባውያን በላይ ተግባራውያን፣ ከልዩነታቸው በላይ አንድነታቸውን፣ ከጎሳ በላይ ሀገርን፣ ከዘመን አመጣሽ ማንነት በላይ ሰውነትን የሚያስቀድሙ ድንቅ ልጆቿ ስለነበሯት ነው።

ውድ አንባቢያን- በዛሬው የሀገሬ አምድ ኢትዮጲያዊነትን የተግባር እንጂ የቃል መገለጫ አለመሆኑን ልጽፍ የተነሳሁበት ዋናው አላማዬ ብዙዎች ኢትዮጲያን ደግመው መጥራት በማይችሉት ውድ ቃል ለብዙ ጊዜ አሞካሽተዋታል አሁን ባለንበት ዘመን እንኳ ሁሉም ስለ ሀገር ፍቅር በያቅጣጫው ይሰብካል ግን እውነት ኢትዮጲያ ሀገሬ ምላሳችን ላይ ናት ወይ? በቀን አስር ጊዜ ኢትዮጲያ ኢትዮጲያ እያልን ለአንድ ደቂቃ ለሀገራችን በተግባር ገልጸናል ወይ? በአንድ ወቅት ከእኔ በእድሜ የሚልቁ ጎልማሳ እንዲህ አሉኝ እውነት ኢትዮጲያን የሚጠራ እና ሀገር እወዳለሁ የሚል ሰው ወንድሙን ይጠላል? የእነሱ አያቶች ለሀገር ደም እና አጥንታቸውን ከፍለው አፍር በሆኑባት ምድር ልጆች ከኔ ቀዬ ሂዱልን ይላሉ እንዴ? እሺ ይህስ ይቅርና እውን ሀገሩን የሚወድ በየመንገዱ ሽንቱን ይሸናል? ቆሻሻ ይጥላል? ሴት ይደፍራል? ወገኑን ይገላል? ይህን ጥያቄ ከሰማሁ ጀመሮ ሁሌም ባዕምሮዬ የሚመላለሰው ነገር ቢኖር ኢትዮጲያዊነት ከምላስ ያልፋል፣ ኢትዮጲያዊነት ከቃል በላይ ነው!! የሚለው ብቻ ነው።

እመኑኝ አሁን ላይ ግለሰቦች ሲገፉን ፣ ግለሰቦች ሲበድሉን፣ ግለሰቦች እንደ ባርያ ሲረግጡን ሀገር አለኝ ወይ ብለን ጠይቀን ይሆናል። ግን ሀቁ በአፈር እና በውሀ ተቦክታ የተሰራች ሳይሆን በደም እና በአጥንት የተገነባች ውብ ሀገር አለችን። ዛሬ እንደ ፋሽን እያየን የእገሌ ብሄር፣ የእገሌ ጎሳ እያልን የምንከፋፈለው በዚሁ ከቀጠለ የእገሌ ቤተሰብ፣ የእነ እንትና ሰፈር እያለ እየወረደ ወደ ግለሰቦች ማንነት መምጣቱ አይቀርም። ለዛም ነው አሁን ለኛ ብቸኛው መድኃኒት ቆም ብሎ ማሰብ እና ስለ ሀገራችን አንድነት መዝመት መሆን ያለበት።

እስቲ ለደቂቃ ዝናብ እየወረደበት አርሶ እና ጭቃ የጠገበ ጋቢውን ለብሶ ለኛ ውበት የሰጠንን ገበሬ አባት እናስብ፣ ብርድ እና ጸሀይ ተፈራርቆባቸው የኛን የማያልቅ ፍላጎት ለመሙላት የመከራ በትር የቀመሱትን እናቶች እናስባቸው፣ የወንድም እህታቸውን ነገ ለማሳመር ብለው በየአረብ ሀገሩ የሚሰቃዩን እንስቶች እናስብ፣ ከውሻ ተሻምቶ የሚመገበው ጎዳና ተዳዳሪ ወጣት እናስብ። አማራ ፣ ኦሮሞ፣ ሲዳማ፣ አፋር፣ ትግሬ፣ ሱማሌ፣ ጋምቤላ፣ ቤንሻንጉል፣ጉራጌ እና ሀረሪ ሳይባሉ ኢትዮጲያዊ በመሆናቸው ብቻ በሜድትርንያን ባህር እና በሊቢያ በርሀ መከራ ለሚቀበሉት እናስብ!! እውነት ሀገራችንን የምንወዳት ከሆነ በማህበራዊ ሚድያ ኢትዮጲያ ኢትዮጲያ ከማለት አልፈን ለችግራችን መፍትሄ የሚሆን ተግባር እንስራላት። ኢትዮጵያ አስለቃሽ ሳይሆን እንባ ጠራጊ ነው ያጣችው። ሀገሬ ተናጋሪ ሳይሆን ሰሪ ነው ያጣችው፣ ውሀ እንዳለ የሚያሳያት ሳይሆን የሚያጠጣት ልጅ ነው ምትፈልገው፣ ስለ አንድነት የሚያወራ ሳይሆን አንድ የሚያረገን ትውልድ ነው ያጣነው።

አውን የመጣው ክፉ ቀን ሊያስተዛዝበን እንጂ ሊያቀያይመን አይደለም። በቀላሉ መንገድ እየሄድን አደናቅፎን ብንወድቅ ‹‹ እኔን›› ብሎ የሚያነሳን እጅ ኢትዮጲያዊ ነው። አቦሌሳ ብሎ የሚያነሳን የኦሮሞ ልጅ ኢትዮጲያዊ ነው፣ ‹‹ሓወይ›› ብሎ ክንዳችንን ይዞ የሚረዳን የትግሬው ልጅ ኢትዮጲያዊ ነው።

ሁሉም የሀገሬ ልጅ እዚህ የደረሰው ከልዩነቱ በላይ አንድነቱን አስቦ እንጂ በሁሉም አንድ ሆኖ አይደለም። አሁን ጊዜው የቃል ሽንገላ ሳይሆን የተግባር ፈተና ነው - ስለ ኢትዮጲያዊነት የምንፈተንበት!! አዎ!! ብዙዎች በዘመናቸው ታሪክ ባይሰሩም በትንሹም ቢሆን ዘመናቸውን አቀርቅረው የታሪክ ሰሪዎችን ጀግንነት በብዕር ሰድረዋል። እኛም ከምላስ ያላለፈ የሀገር ፍቅራችንን ታሪክ መስራት ባንችል ለትውልድ የሚጻፍ ስራ እንስራ።

ሀገር መውደድ የሚጀመረው እራስን ከማየት ነው። እስቲ ራሳችንን በብሄር ሳይሆን በሰውነት መነጽር መመልከት እንጀምር- ሰው መሆናችን ሲገባን ለሌላው የሰው ፍጥረት ክብር ይኖረናል። ያ የሀገር ፍቅር መጀመሪያ ነው። በቃላት ያሽሞነሞነውን ሀገር በተግባር እንኑር። እኛ ደልቶን ምግብ ስናማርጥ በርሀብ አለንጋ የሚገረፈውን ወገን ምን ላርግለት ማለት እንጀምር። እኛ በብዙ ሺህ ብሮች የሚዋብ አልጋ ለማማረጥ ስናስብ ለደቂቃ ካርቶን አንጥፎ ስለሚተኛው የጎዳና ልጅ ወንድማችን እናስብ። የምንቀባውን ሽቶ ስናማርጥ እስቲ በብርድ ልጅ ታቅፋ በቆሎ ስለምትሸጠው ኢትዮጲያዊ እናስብ፣ ስለምንጠጣው ውስኪ ስንጨነቅ ምነው ለደቂቃ የሚጠጣ ውሀ ላጡት እህት ወንድሞቻን ብንጨነቅ? ለኔ ኢትዮጲያዊነት ከምላስ አልፎ ልብ ላይ የተሰራ የተግባር ትምህርት ቤት ነው። ለዚህም ምስክሬ ከራሳቸው ምቾት እና ደስታ በላይ ለኛ ሲሉ ደምና አጥንታቸውን የሰጡልን አያቶቻችን ማስታወስ በቂ ነው። እኛ ዛሬ ቀና ብለን እንድንሄድ እነሱ ትናንት እግርና እጃቸውን አጥተው ጎዳና ላይ ወድቀው እኛን ፍርፋሪ ይለምናሉ፤ ከዘህ በላይ ምስክር አልሻም!! አዎ ሀገር መውደድን የምለካው በሽሙንሙን ቃላት ኢትዮጲያን በማሞካሸት ሳይሆን እያንዳንዷን ስራ እና ተግባራችን ለወገን መለወጥ፣ አንድነት፣ ፍቅር በመስጠት ሲሆን ነው።

ለዛሬው ጽሑፌ መቋጫ ይሆነኝ ዘንድ ‹አጼ ሚኒሊክ እና የኢትዮጲያ አንድነት› በተክለጻዲቅ መኩሪያ የተጻፈ መጽሀፍ አጣቅሼ የሀገር ፍቅርን በውብ ቃላት ብቻ ሳይሆን በውብ ተግባር ጽፈው ካለፉት ኢትዮጲያዊ እና ከምላስ ያለፈ የልብ ተግባር መሆኑን ካሳዩን ጀግኖች መካከል ደጃዝማች ባልቻ ሳፎን በጨረፍታ ላንሳ እና በግጥም ልሰናበታችሁ።

## ደጃዝማች ባልቻ ሳፎ

ባልቻ የፈረስ ስማቸው አባ ነፍሶ ነው። በልጅነታቸው ከጦርነት ላይ ተማርከው በአጼ-ሚኒሊክ ቤት ያደጉ ታማኝ የጦር መኮንን ነበሩ። ብዙ ግዜ በጅሮንድ ተብለው የንብረት ሀላ ሆነው ሰርተዋል። የበለጠ እንደረስ አባተ የሚታወቁት በወታደራዊ መስክ ነው ። በመቀሌው እና በዓደዋው ጦርነት በጀግንነት ተዋግተው ስመጥርነት አግኝተዋል። ከአድዋ መልስ በደጃዝማችነት ማዕረግ ሲዳሞን ሌላ ግዜ ሀረርጌን ተሸመው አስተዳድረዋል። በንግስት ዘውዲቱ ዘመን በክብር እና በታላቅ ማዕረግ ሲኖሩ ከቀዳማዊ ኃይለስላሴ ስላሴ ጋ ስምምነት ስለአልነበራቸው ብዙውን ግዚያቸውን በግዞት አሳልፈዋል። በ1928 ዓ.ም የኢጣልያ ፋሺስት የዓድዋውን ብድር ለመመለስ በተዋጋበትና አዲስ አበባ በያዘበት ጊዜ በ80 ዓመት ዕድሚያቸው በአርበኝነት ዘመቱ ‹‹ ቀዳማዊ ኃይለስላሴ ያልቻሉትን ጠላት እርሶ ሊመልሱት አይችሉም እና ለኢጣሊያ ቢገቡ ይሻላል›› ብለው ቢመክሯቸው ‹‹ ሽምግያለሁ መሞቴ እንደሁ አይቀር በሰማይ ላይ ጌታዬ ሚኒሊክ በኢትዮጲያ ዙፋኔ ላይ ማነው የጠቀመጠው ብለው ቢጠይቁኝ ምን ብዬ መልሳለሁ›› የሚል ቃል ወርውረው በሽምግልና እና የክብር ካባ ለብሰው በመጦሪያቸው ከምንም በፊት ሀገሬን ብለው ከቃል በላይ በተግባር የኖሩላትን ሀገራቸውን ለጠላት ላለመስጠት ልክ እንደ ወጣት በ80 ዓመታቸው በወጨጫ ከጣሊያን ጋር ተዋግተው ሞቱ። ይህ ነው የሀገር ፍቅር ልክ ከቃል በላይ በመኖር ሲገለጽ በርግጥ በአሁን ሰዓት የጦር ሜዳ ጀግንነትን ሳይሆን የሀሳብ፣ የአንድነት፣ የሀገር ፍቅር ጅግንነትን እንሻለን።

አትዮጲያ
(ካነበብኩት)
ይብላኝለት እንጂ.....
በዘር ተከፋፍሎ፤ ለፈረሰው ቤቷ
ይብላኝለት እንጂ........
በሰው ሰራሽ ደዌ፤ ለካዳት ጉልበቷ
ይብላኝለት እንጂ...
ተሸርፎ ተኮርሶ፤ ላለቀ መሬቷ
ይብላኝለት እንጂ...
ጸጉሯን ስትነጭ፤ ለገጠበው እናቷ
ይብላኝለት እንጂ...
ባዘን ለገረጣው፤ ማድያታም ፊቷ
ይብላኝለት እንጂ...
ለዘር ደዌ በሽታ፤ ላስቀራት ባጥንቷ
ይብላኝለት እንጂ...
ካልጋ ላቆራኛት፤ መጋኛ ልክፍቷ
ከዚህ ሁሉ ኋላም...........
የደስደሷ እረግፎ፤ ከስታና ጠውልጋ
የዘመን ጥላሸት መልኳን ተለቅልቃ
የወየበ ፊቷን፤ ገጻ ላይ አጥልቃ
ቁንጅና እርቋት፤ ፉንጋነትን ታጥቃ
ልንጠላት አንችልም ውብ ሀገር ነች በቃ!!!

‹‹ መልካም እና ሰላማዊ ሆነን ከተዋደድን በፍቅር የማይመለስ የለም ››
ኢትዮጲያ ለዘላለም በህዝቦቿ ፍቅር ትኑር...........
በቀጣይ በሌላ የሀገሬ ጽሁፍ እስከምንገናኝ እያንዳንዷ ቀን እና ሰዓት ለወገናችን አንድነት፣ፍቅር፣ስኬት የምንሰራበት እንዲሆን ተመኘሁ።



በሀና ሀይሉ
( hanahailu016@gmail.com)

# የግል መለያ
# " PERSONAL BRANDING "

ቢዝነስ ኢንሳይደር ላይ የወጣው መረጃ እንደሚለው ባለፈው አመት የአፕል ብራንድ 146.3 ቢሊየን፡ዶላር ዋጋ የአማዞን ብራንድ ደግሞ 150.8 ቢሊዮን ዶላር እንደሚያወጣ ዘግቦ ነበር! አንዳንድ ጊዜ የድርጅቶች ስም ከራሱ ከድርጅቱ የበለጠ ዋጋ ያወጣሉ! የኛስ ዋጋ ምን ያህል ነው?
ሰዎች እኛን እንዴት ያዩናል?
ከስማችን በተጨማሪ ስላካቸው ላይ ማን ብለው መዘገቡን? በምን አይነት መልኩ ነው ሰዎች እንዲያስታውሱን የምንፈልገው?

ፈልገንም ይሁን ሳንፈልግ ሰዎች ከስማችን ቀጥሎ እኛን ለመለየት ሌላ ተጨማሪ መለያዎችን ይፈጥሩልናል! መለያ/Brand የሚለው ቃል በጥንት ዘመን ሰዎች ከብቶቻቸውን ለመለየት ብረት በእሳት አቃጥለው ምልክት ሲያደርጉበት ማቃጠል/burnt ተብሎ ነበር የተጀመረው! ከዛ በኋላ ብዙ ድርጅቶች ምርት እና አገልግሎታቸውን ከሌላ ድርጅት ይበልጥ በሰዎች ዘንድ እንዲታወስ እና እንዲታወቅ ብዙ ይጥራሉ ገንዘባቸውንም ያፈሳሉ! መለያ/Brand ማለት ምስል፥ ስራ ፥አላማህ ፥ቀለም ፥ባህሪ ፥አገልግሎት ወ.ዘ.ተ ሲሆን በተደጋጋሚ በህይወታችን ውስጥ ሲንፀባረቅ ሰዎች በቀላሉ እንዲያስታውሱት ይሆናል! በደንብ ለመለየት ቀጥሎ ያሉትን ቃል-ምልልሶች ያንብቡ
አቤል የዩኒቨርስቲ ተማሪ ነው
ለምሳሌ
1:- አቤል እኮ ፈተናውን አለፈ?
2:-አቤል የቱ ባለቀይ ሱሪው?
1:-አረ አይደለም
2:-ሱሰኛው?
1:-አዎ
3:-በጣም ይገርማል እንዴት አለፈ በናትህ

በዚህ ቃለ ምልልስ ውስጥ አቤልን ከሌላው ለመለየት ቀይ ሱሪ. ...ሱሰኛ....እንደ አማራጭ ቀርቧል! ሌላው በትንሹም ቢሆን ሱሰኛ የሆነ ሰው ፈተና ማለፉ አስገራሚ ሆኖ ተስሏል!
በተለምዶ አንዳንድ ነገሮች ላይ ስማችን ሲበላሽ የሌላውንም ስራችንን አብሮ ያደበዝዘዋል፤ ስርተንም ቢሆን የማንሰራ ተደርጎ ይቆጠራል።
እናንተ በየትኛው ነው መጠራት የምትፈልጉት?

በአንድም ይሁን በሌላ መልኩ ፈልገንም ይሁን ሳንፈልግ ሰዎች ተጨማሪ መጠሪያዎችን፣ ከውሎአችን ፣ አመለካከታችን፣ ንግግራችን ፣አለባበሳችን ላይ ተመርኩዘው መለያ ይፈጥሩልናል!

ይሄንን ነገር ካወቅኩበት ጊዜ አንስቶ ግላዊ እና ሞያዊ እድገቴን ለማሻሻል በተለያየ መልኩ ስሰራ ቆይቻለሁ! ምዕራባዊያም "ሶስት አይነት መነፅር አለ"ይላሉ። የመጀመሪያው ሰዎች እኛን የሚያዩበት መነፅር ነው! ብዙ ጊዜ ሰዎች ከውጪ በሚያዩት እና ከሌሎች በሚሰሙት ነገር ለኛ ያላቸውን አመለካከት ይለዋውጡታል! ጥሩ መጥፎም ቢሆን ትክክልም ቢሆን ከሁሉ በፊት አይናቸው ከዛም ጆሯቸው ስለማንነታችም ዳኛ ይሆናል።
ሁለተኛው እኛ ለራሳችን ያለን እይታ ነው! እንደ ድክመታችን እና ጥንካሬያችን ለራሳችን ያለን አመለካከት ይቀንሳል፣ ይጨምራል. ..ይወርዳል ፣ ይወጣል። ስለዚህ ስለራሳችን ባወቅንበት ልክ የሚመዘን ለራሳችን ያለን እይታ ነው
ሶስተኛው ትክክለኛው ማንነታችን የሚታይበት መነፅር ሲሆን ብዙ ጊዜ እኛም ራሳችንን ሳናውቅ፣ ሳንገነዘብ ልንሰነብት አልያም ልንሞትም እንችላለን። ቢሆንም እንደሰውም እንደራስም እይታ ላይሆን የሚችል ማንነት ሊኖረንም ይችላል!
ሰዎች እኛበምንፈልገው መልኩ እንዲያስታውሱን እና እንዲጠሩን የምናደርግበት ሶስት ዋና ዋና ነገሮች እነሆ፦

## 1.ራስን ማወቅ

ከሁሉም ነገር የሚቀድመው መነሻህን እና መድረሻን መለየት....አሁን ያለን አቅም ከወደፊት ፍላጎት ጋር ማዋሀድ። ፍላጎት፣ችሎታ ጥንካሬ እና ድክመት.....እያንዳንዱን ማንነታችንን ለይቶ ማወቅ፤ የራሳችንን መለያ ለመፍጠር ትልቁን ድርሻ ይወስዳል!
ለምሳሌ: - ልዩ በራሷ ላይ ከሰራችው የጥናት ውጤት ተቋደሱልኝ
"ደራሲ ተብዬ ብጠራ ምኞቴ ነው በተለያዩ ጊዜዎች ለፃፍኳቸውን ፅሁፎች ጥሩ አስተያየት ማግኘቴ የስነ-ፅሁፍ ክህሎት እንዳለኝ እንዳውቅ ረድቶኛል" ይሄ ነገር ልዩ ስለራሷ በማጤን ስለችሎታዋ ያገኘችው ፍንጭ ነው!

## 2, ራስን ትክክለኛው ቦታ ላይ ማስቀመጥ

ማንነትን መለየት ሲቀድም መሆን ያለብንን ትክክለኛ ነገር እናውቃለን። እሱን ካወቅን ቦታው ላይ ሆኖ መገኘት ነው!

ለምሳሌ:- ልዩ " የስነ-ፅሁፍ ክህሎት እንዳለኝ ካወኩ በኋላ የተለያዩ ፅሁፎችን ማንበብ መፃፍ እና በየመድረኮቹ ላይ ማቅረብ ጀመርኩ!"
ልዩ በተደጋጋሚ ስነ ፅሁፍ ያለበት ቦታ በመገኘቷ ራሷን እና ስራዎቿን ታስተዋውቃለች።
አዳዲስ እድሎችን እና ግብዣዎችን ታገኛለች።
ከሷ ጋር ተመሳሳይ ችሎታ ያላቸውን ሰዎች በማግኘት ልምድ ሀሳብ መጋራት ትችላለች!

## 3, ራስን ማስተዋወቅ

ራስን ማስተዋወቅ በሀገራችን በአሉታዊ መልኩ ይታያል። ሆኖም ግን አለም ላይ ያሉ የልህቀት መምህራን ራስን የማስተዋወቅን ጥቅም በጥልቀት ያስተምሩታል።
ከላይ በምሳሌው የገለፅናት ልዩ ሰዎች ደራሲ በመሆኗ እንዲያውቋት ከፈለገች አለባበሷን አነጋገሯን እና ሌሎችንም ነገሮች በሙሉ በማስተካከል ራሷ በምትፈልገው መልኩ እንድትታይ እና እንድትገለፅ ይረዳታል!
ስለዚህ ሁል ጊዜ ከስሟ ቀጥሎ ብዙ ጊዜ ስለችሎታዋ ለሰዎች ታስተዋውቃለች! ማህበራዊ ድህረ ገፆቿ እሷ፡ መሆን በምትፈልገው መልኩ በሰዎች ዘንድ ይታያል!
መፅሀፍ ምን በጥበብ የተሞላ ቢሆን ገበያ ላይ ሲወጣ ቀድሞ የሚታየው የውጪ ሽፋኑ ነው! እኛም የፈለገ የበሰለና የመጠቀ እይታ ቢኖረን ሀገር የሚለውጥ ሰነድ አዘጋጅተን አለባበሳችን አነጋገራችን ካላማረ አልያም ማህበራዊ ድህረ ገፃችን ላይ የምንፅፈውን አይተው ሊሰሙን እንኳን ላይፈቅዱ ይችላሉ።
አዎ ወገን ለመደገፍ የሚሆን ሰነድ ይዘህ እየዞርክ ፌስቡክህ ላይ ድንጋይ ስለማንሳት ሀገር ስለማጥፋት የተፃፈውን ከተጋራህ ከለጠፍክ ማን ያምንሀል?
በነገራችን ላይ በልጅነቱ ጥቁር ህዝቦችን የሚያንቋሽሽ ነገር አድርጎ ፎቶ በመነሳቱ እና እሱ ምስል በመለቀቁ ከምርጫ የታገደ መሪ እንዳለ በቅርብ ሰምቼ ነበር።
ስለዚህ መለያችን ምስላችን ነው። ዛሬ የምንታይበት መንገድ ለነገ በር ይከፍታል ወይም ሊከፈት የነበረውን ይዘጋል።

በልብሳችንም ቢሆን ማንነታችንን እንደሚገለፅ ልናስተውል ይገባል!
ሰውም ልክ እንደዛው ነው፤ እንዴት ካላችሁ መልካም።
ልብ ብላችሁ ከሆነ አንድ ፕሮግራም ሲዘጋጅ ፕሮግራሙ ላይ ከሚቀርበው እና ከሚያቀርበው ሰው ይልቅ ተጋብዞ ይመጣል የተባለ እንግዳ ትኩረት ይሰጠዋል፤ ያውም እንግዳ ሆኖ ሊመለከት ብቻ ይሆናል የሚመጣው።
ነገር ግን ከተለፋበት ፕሮግራም በላይ የአንድ ሰው ስም ትልቅ ዋጋ ያለው መለያው በሰዎች ላይ የሚፈጥረው ትልቅ ተፅኖ ስላለ ነው!
ወደድንም ጠላንም የራሳችንን መለያ ይኖረናል!
ይሄ ነገር አሳስቦን ከሰራንበት ስማችንን ብቻ ስራ ፣የገቢ ማስገኛ ፣ ክብር ይሆናል። ካልሰራንበት እና ካልተጠነቀቅንለት ግን ያከስረናል!!

የግል መለያቸው ላይ የሰሩ ሰዎች
የራሳቸው የሆነ የግል ፋሽን/አለባበስ
የሚወዱት እና የሚጠቀሙበት ቀለም
የሚወዱት እና የሚፈልጉት....

የስራ ዘርፍ
ሙያዊ ከሆነ ደግሞ ቢዝነስ ካርድ፣ የሶሻል ሚዲያ (በትክክለኛ ስማቸው ወይም መጠራት በሚፈልጉበት ስም) ከዛም ሲያልፍ ጎግል ላይ :የሚገኙበትን መንገድ ይፈጥራሉ!
ባጠቃላይ ከውስጥ ያለንን አቅም ችሎታ ለማጉላት በሰዎች ዘንድ የምንታይበትን እይታ መነፅር ማስተካከል እንደሚገባን አምናለሁ!
ውስጣችንም ሆነ ውጪያችንን በማስተካከል ለራሳችን የተሻለ ማንነት መፍጠር ዋጋችንም ከፍ ማድረግ እንችላለን ባይ ነኝ!

__________ሰላም ለእናንተ_________



kendilMobile APP

ቀንዲል ዲጂታል መፅሔት ከኢትዮ ስፓርክ ጋር በመተባበር መፅሔታችንን በሞባይል መተግበርያ በልዩ አቀራረብ ወደ እናንተ ለማድረስ ዝግጅታችንን አጠናቀናል።
መተግበርያውን በማውረድ እና ተንቀሳቃሽ ስልካችሁ ላይ በመጫን በየወሩ የሚለቀቁትን የመፅሔታችንን አምዶች በስልኮቻችሁ ላይ በቀላሉ መከታተል ይችላሉ።
መተግበርያውን የቴሌግራም አድራሻችን ላይ ያገኙታል። @kendilM



ሰለሞን ለማ {ሶልጅት} ሰርከስ ኢትዮጵያ ካፈራቻቸው በርካታ ኢንተርናሽናል የሰርከስ አርቲስቶች አንዱ ነው። በበርካታ የአውሮፓ ሚድያዎች እና ድህረ-ገጾች ላይ ሰለሞን ሶልጅት በመባል የሚታወቀው ሰለሞን ለማ ገ/ፃዲቅ ትውልዱ አዲስ አበባ ሲሆን እድገቱ ደግሞ በአዳማ ከተማ ነው። ሰርከስ ናዝሬትን በ9 አመቱ ተቀላቅሎ ከ11 አመታት በላይ ባለው ተሰጦ ሲያገለግል የቆየ ሲሆን ከኢትይዮጵያ ከተመረጡ ጥቂት አርቲስቶች ጋር በመሆንም በቻይና "China wuqiao international college" ተመርቋል። እንዲሁም ከ6 ኢትዮጵያውያን ጋር በመሆን "አቢሲኒያ Jugglers" የተባለ ቡድን በመመስረት በተለያዩ የአለም ሃገራት ፣ በኤዥያ ፣ በአውሮፓ እና በአሜሪካ እጅግ በርካታ በሆኑ ከተሞች ላይ የኢትዮጵያን ባህል እና ስም ሲያስጠሩ ቆይቷል። ሰለሞን በአሁኑ ሰአት በአለም ትልቁ እና የመጀመርያው በሆነው cirque du Solei Company ውስጥ እየሰራ ይገኛል። እኛም በቀጥታ ከጄኔቫ ቃለ-መጠይቅ አድርገን በዛሬው የቀንዲል መጽሄት የአውደ ብሩሀን ገጽ እንግዳችን አድርገነዋል፤ መልካም ንባብ!!

**ቀንዲል**:- በመጀመሪያ የዛሬው የቀንዲል መጽሄት የአውደ ብሩሀን ገጽ እንግዳችን በመሆንህ በቀንዲል መጽሄት ስም ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

***ሰለሞን***:- እኔም በመካከላችን ያለው የሃገራት እና የብዙ ማይሎች እርቀት ሳይገድባችሁ ካለሁበት ፈልጋችሁ እንግዳችሁ ስላረጋችሁኝ ከልብ አመሰግናለው።

**ቀንዲል**፡- እሺ አመሰግናለሁ ሰለሞን። በቀጥታ ወደ ጥያቄዎቼ ልሂድ። ከአጀማመርህ እንነሳና ወደ ሰርከስ ጥበብ እንዴት ልትገባና እንዴት የሰርከስ ጥበብን እንደ ሞያ ልትይዘው ቻልክ ?

***ሰለሞን***:- የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርቴን የተከታተልኩት በናዝሬት ቁጥር 4 ትምህርት ቤት ነው። እናም በዛን ጊዜ ከየክፍሉ የተወጣጡ በርካታ ህጻናት አንድአይነት ቲሸርት በመልበስ ተመሳሳይ የሆነ የስፖርት እንቅስቃሴ {ጂር ጂር} ነበር የምንለው እንቅስቃሴው በፊሽካ ይታገዝ ስለነበር። እናም በትላልቅ በአላት ላይ በስቴድዮም በሚዘጋጁ ትላልቅ ዝግጅቶች ላይ እናቀርብ ነበር። ታድያ በአንድ የበአል ቀን እዛው ስቴድዮም ውስጥ የሰርከስ ናዝሬት ትርኢትን ለማየት ቻልኩኝ፡ ያየሁትንም ማመን አልቻልኩም ነበር ። አንድ ሰው ገመድ ላይ ቆሞ እንዴት ሙሉ ልብስ ሊቀይር ቻለ ብዬ ተደነቅኩኝ። የዛን ቀን ታዳያ ያየሁት የሰርከስ ናዝሬት ትርኢት ለመጀመርያም ጊዜ ስለሆነ እስካሁን ከአይምሮዬ አልጠፋም ። በተለያዩ በኢትዮጵያ የብሄር ብሔረሰቦች ልብሶች እና ደማቅ ቀለማት ያሸበረቁ ውብ ልጆች ፍጥነትና ቅልጥፍና ፣ የሙዚቃው መቀያየር ፣ በዋሽንት፡ በክራር ፣ በማሲንቆ እና በከበሮ የተቃኘተው የሙዚቃው ቅንብር እና ውህደት በቃ ልጅም ስለነበርኩኝ ከዚ ሌላ ሙያ ከዚ ሌላ አለም የለም ብዬ አሰብኩ። ሰርከስ ናዝሬትን ተቀላቀልኩኝ፡ ሰርከስ ናዝሬትንም ለአንድ ታዳጊ አስፈላጊ የሆኑትን የአካል እና የአእምሮ ክህሎቶችን እንዲሁም እስካሁን የምጠቀምባቸውን የህይወት ተሞክሮዎች ልምድ ለውጦችን በማከል አሳደገኝ።

**ቀንዲል**:- ወጣትነት ላንተ ምንድነው?

ሰለሞን፡-ወጣትነት በአንድ የሰው የህይወት ዘመን ውስጥ ወሳኙ ጊዜ ሲሆን ለአንድ ሃገርም የጀርባ አጥንት ነው። ሃገር ያለወጣት መኪና ያለ ነዳጅ ማለት ነው። ወጣትነት ብዙ የመንገድ አቅጣጫ ተቃውመህ መንገድ ላይ ደርሰህ የወደፊት ማንነትህን ለመወሰን የምትወጥንበት ፈታኝ ጊዜም ነው። ወጣትነት ከባድ ሃይልም ነው። ኒውክሌር በይው {...ሳቅ...} ወጣትነት በመልካም አስተሳሰብ ስንደመር ለአለም መልካም አስተዋፅኦ የምናበረክትበት ፣ በመጥፎ አይዲዮሎጂ ደሞ ለሃገርም ለአለምም ችግር የምንሆንበት ከባድ ሃይል ነው። ብቻ ወጣትነት ያንተን ፡ የቤተሰብህን እና የሃገርህን ሁኔታ ሊቀይር የሚችል ጎል የምታስቀምጥበት፣ ለዛም ሙሉ አቅም የተሰጠህ ወሳኝ ጊዜ ነው።

# #የአውደብሩሀን ገፆች



**ቀንዲል**፦ ሰርከስ በኢትዮጵያን ውስጥ ስሙ ይታወቃል? እስኪ ለአንባቢዎቻችን የሰርከሰን ትክክለኛ ትርጎም ንገረን።

***ሰለሞን***፦ መልካም። ሰረከስ በኢትዮጵያ ረጅም እድሜ ሊኖረው ይችላል ግን Marc La Chance 1991 ወደ ኢትዮጵያ ከመጣ በሁዋላ ነው ከፍተኛ የሰርከስ እንክስቃሴ የታየው፡ Marc ለሰርከስ በኢትዮጲያ ብዙ ድጋፍ አድርጓል። በጅማ በመቀሌ በናዝሬት ትላልቅ የሰርከስ ፌስቲቫሎች ተካሄዶ ነው ሰርከስ በአጭር ጊዜ በጣም ተወዳጅነት እና እውቅና ያገኘው።
በውጭው አለም ሰርከስ አንድ ምእተ አመት አልፎታል ሲጀመርም ነገስታት ሰውን እና የዱር እንሥሳትን በታጠረ ክብ መድረክ ላይ በማስገባት በፍልሚያው የሚዝናናበት ነበር። ከዛም ተነስተው ሰዎች እንስሳቶችን በማላመድ ወደ ትርኢት በመቀየር እስካሁን በዛ መልክ እንደ እንድ ባህል መቅረቡን ቀጥሏል። ሰርከስ ማለት እንግዲህ “Circle” ከሚለው ቃል የመጣ ሲሁን ያም በጥንት ግዜ ሰዎች እንስት የሚፋለሙበት መድረክ ክብ ስለነበር ማለት ነው።
ሰርከስ በአሁን ጊዜ በአለም ላይ ያለበት ደረጃ እጅግ አስደናቂ ነው በመደረኩ ከሚቀርቡ ትርኢቶች በተጨማሬ በተለያየ ድርጅቶች የቴክኖሎጂ ውድድርንም ያካተተ ነው። እንድ የሰርከስ ትሪኢት በመብራት ፡ በድምጽ፡ በውሃ ፡ በእሳት ቴክኖሎጂ የታገዘ ነው።

**ቀንዲል**:- አሁን ስለገባህበት በአለማችን ላይ ትልቅ የስለሆነ የሰርከስ ድርጅት ንገረን?

***ሰለሞን***:-አሁን የምሰራበት የሰርከስ ድርጅት ሰርከስ ዱ ሶሌ ይባላል በአለማችን ቴክኖሎጂን እና የሰርከስ ትርኢትን በማዋሃድ በአለም እስካሁን ይመራል። ተቀማጭነቱ በካናዳ ሲሆን በተለያዩ የአለም ሃገራት ላይ በጣም ትላልቅ ትሪቶችን ያካሂዳል። 5,000 ሰራተኞች ሲኖሩት 1500ዎቹ ከአለም የተወጣጡ አርቲስቶች ናቸው። እኔም የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ በመሆን ድርጀቱ በተመሰረተ በ35 አመቱ ለመቀላቀል ችያለሁ።

**ቀንዲል**፦ የህይወት መርሄ ነው የምትለው ነገር ካለ ብታካፍለን ?

***ሰለሞን***፦ የኔ የህይወት መርህ የመጀመሪያው፦ ፈተናዎችን እና መሰናክሎችን ወይም ብዙ ተስፋ ያደረኩባቸው ነገሮች ሳይሳኩ ሲቀሩ እኔ ለኔ ካሰብኩት በላይ ፈጣሪ ለኔ ያሰበልኝ ይበልጣል በሚል በፈተናዎች ከመደናገጥ እና ተስፋ ከመቁረጥ ክስተቶችን በበጎ በመመልከት ለወደፊት መማሪያ ማድረግ ነው። ። ሌላው እራስን መግዛት፣ (self-discipline) እራስን መጠበቅ እና እራስን መውደድ ናቸው።

**ቀንዲል**:- እራስን መወደድ ስትል እስኪ አብራራልን።

***ሰለሞን***:-እራሰን መዉደድ ስል "እራስ ወዳድ" ከሚለዉን ትርጎም እጅግ የተለየ ነው። ይሄ የኔ የግል መርህ እና አስተሳሰብ ነው። በኔ አመለካከት አንድ ሰው እራሱን ካከበረ እና ከወደደ አዲስ እሳቤዎችን ለመቀበል ፣ከሌሎች ሰዎች ጋርም በህብረት ለመስራት ፣ ለሌላውም ፍቅርን ለመስጠትም አይገደብም የሚል ነው።

**ቀንዲል**:- ብዙ ወጣቶች አንድን ነገር ጀምረው ማህበረሰቡ ካልደገፈው እና የሚያግዛቸው ከሌለ መሆን የሚፈልጉትን ትተው ሌላ አማራጭ ይሞክራሉ። አንተ ግን ከመነሻህ ጀምሮ ይሄን ሁሉ ርቀት በፅናት የተጓዝክበት የዚህ ሁሉ ስኬቴ ሚስጥር ምንድነው ትላለህ?

***ሰለሞን***:- እውነት ነው!! በዚ በኩል ከባድ ተጽኖ አለ። የሰው ዘር በሙሉ የተለያየ መክሊት ተቀብሎ ነው ይህችን አለም የሚቀላቀለው። ሁላችንም አንድ አይነት ሃሳብ አንድ አይነት ስራ ሊኖረን አይችልም። ዶክተሩ ፣ ኤሌትሪክ ሰሪ ሊፈልግ ይችላል፡ ኤሌትሪክ ሰሪው ደሞ ምግብ አብሳይ ፣ ከጥቂት አመታት በፊት የወንድ የምግብ አብሳይ አይታወቅም ነበር። እስቲ አስቢው በአንድ የተከበረ ቤተሰብ ውስጥ ልጄ ዶክተር ወይም አውሮፕላን አብራሪ ይሆንልኛል ብሎ በሚያስብ ቤተሰብ ውስጥ ልጁ ተነስቶ እኔ ሳድግ ወጥ ሰሪ ነው የምሆነው ቢል፡ ምን አልባት ይሄ ልጅ አብዷል እንዴ? ይባል ይሆናል። ዛሬ በአለማችን በሚሊየን የሚቆጠሩ ተከታይ ያላቸው በግል አውሮፕላናቸው ከሃገር ወደ ሃገር እየተዘዋወሩ የምግብ ዝግጅት የሚያቀርቡ ታዋቂ ሰዎች አሉ። ምንም ይሁን ምን የሚናቅ ሃሳብ የለም፤ በምንም መስክ ከወደድሽው እና ከልብሽ ከሆነ በዛ አቅጣጫ ከምርጦች አንዱ የማትሆኚበት ምክንያት የለም። በርግጥ ብዙ የማይመቻቹ ነገሮች ሊኖሩ ይችላሉ
የኔ ተሞክሮም ይህንን የሚያሳይ ይመስለኛል። ይህንን የመገለባበጥ እና የሰርከስ ፍቅር እንደጀማመረኝ ከጥቂት ጎረቤቶቼ በስተቀር ብዙም ሰው የሚደግፈኝ አልነበረም።



እንዳድ ሰዎች እንደውም ባያበረታቱ እና ዝም ቢሉ መልካም ነበር ግን ሞራልን የሚያዳክም ነገር ይናገራሉ። "አንተ ተሰብረህ የሰው ሽክም ለመሆን ነው አይደል?"። አርፈህ አተቀመጥም? {...ሳቅ...} ብቻ ብዙ ብዙ። ያ እኔን ካለምኩበት አላስቀረኝም፤ እጅግ ብዙ ለፍቻለሁ ትግስት አስጨራሽ ግዝያትን አሳልፌያለሁ። ብዙ ግዜ ከትምህርት ቤት ወጥቼ ምሳ ሳልበላ ሰርከስ በመለማመድ ያሳለፍኩባቸው ቀናቶች በጣም በርካታ ናቸው።
ብቻ ነገሮች ባልተመቻቹበት ሁኔታ ውስጥ በመሆን ከዉስጥህ መሆን የምትፈልገውን ለመሆን እና ግብህን ለመምታት የሚያጋጥሙ መሰናክሎችን ለመጋፈጥ ምንያህል ዝግጁ ነህ? ያለምክለት እና የታገልክለት ያንተ መክሊት መልሶ ይከፍልሃል።

**ቀንዲል**:- ሰርከስ ብቻ ሳይሆን የማጂክ/ እኛ ምትሀት የምንለው አይነት አስደናቂ ትዕይንቶችን ስታሳይ በአለም አቀፍ መድረክ ላይ ያዩህ ሰዎች ትልቅ አድናቆትን ሰጥተውሀል። ይሄ ጥበብ በሀገራችን ምን ያህል ተቀባይነት አለው? የማጂክ ወይም ምትሀት አንድ የጥበብ አካል ነው?

***ሰለሞን***:- አዎ። አንዳንድ የማጂክ ትሪኮችን እሰራለሁ። ያው እንዳድ ጊዜ ብቻ መድረኮቹ ለሰርከስ ትሪኢት የማይመቹ ሲሆኑ የማጂክ ትሬኢቶችን አቀርባለው። በዚ መስክ እንኳን ብዙም አልገፋሁበትም ማጂክ ብዙ ጊዜ እና ጥናት ይፈልጋል ። ኢትዮጵያ ዉስጥ ተቀባይነት አለው ወይ? አይመስለኝም። ማጂክ ትሪክ- ምትሀት ወይም አስማት አለመሆኑን ህብረተሰረቡ ሊረዳ ይገባል። ማጂክ ትሪክ ምትሀት ሳይሆን የተጠና ጥበብ ነው። ለምሳሌ እኔ ላስቬጋስ ላይ ከሌሎች ሶስት አርቲስቶች ጋር በመሆን "ኪውክ ቼንጅ" የሚባል ማጂክ ተምሬ ነበር። ያም በ3 ሰከንድ ውስጥ ሙሉ እና የተለያዩ ልብሶችን መቀየር ነው። ለምሳሌ የለበስኩትን ጥቁር ሱፍ መድረክ ላይ በ3 ሰከንድ ዉስጥ ወደነጭ እቀይረዋለው። እንዴት? ያ ሚስጥር ነው። ይህንን በምርምር አስበው በብዙ ልፋት የፈጠሩት አርቲስቶች ሚስጥሩን ይጠብቃሉ፤ ሲያስተላልፉም በጣም በጥንቃቄ እና በጣም በውድ ነው።

**ቀንዲል**:- ኢትዮጲያዊነትን እና ኢትዮጵያን እንዴት ትገልፃቸዋለህ?

***ሰለሞን***:-ኢትዮጲያዊነትን እንዲ በአጭሮ የሚገለጽ አይደለም፤ ኢትዮጲያዊነት ጥልቅ ነው። በአንድ ወቅት በጣም የማከብራቸው ፕሮፌሰር ኃይሌ ገሪማ ቃለምልልስ ላይ የተናገሩትን ብደግምልሽ ደስ ይለኛል።
"ኢትዮጲያዊነትን የምትችልበትን፣ ጽፈህ ፣ ስለህ ፣ ዘምረህ መልካም ሰርተህ ማለፍ ነው። ኢትዮጵያ ደሞ ባንተ ያልተጀመረች ባንተም የማትጨረስ የምትቀጥል ናት ።"

**ቀንዲል**:- ካነበብካቸው መጽሃፍት ውስጥ የሰዎች ህይወት እድገት ላይ ተፅኖ ይፈጥራል የምትለውን እንዱን እስቲ ለአንባቢያን ጠቁምልን?

***ሰለሞን***:- አዎ!! ብዙ የማንበብ ፍላጎት ቢኖረኝም ሩጫ ይበዛብኛል። ሆኖም በቻልኩት መጠን አነባለሁ። እንድ ጥቀስ ካልሽኝ "The power of now" የሁል ጊዜ ምርጫዬ ነው።
**ቀንዲል**:- ከረዥም ጊዜ በኋላ ወደ ሀገርህ ተመልሰህ የማህበረሰብ እድገት ላይ የሚሰራ ሰኒኮ የሚባል ግብረሰናይ ድርጅት እንዲመሰረት አድርገሀል። እስኪ ስለድርጅቱ ንገረን?
ሰለሞን፡-አመሰግናለሁ!! ይህ የበጎ አድራጎት ድርጅት ሃሳብ የረጅም ህልምና እቅዴ ነበር።

## #የአውደብሩሀን ገፆች



አሁን ለመልካም ጓደኞቼና ለመልካም አሳቢ ሰዎች ምስጋና ይግባቸውና ሀሳቤ ከሃሳብነቱ አልፎ ወደመሬት ወርዶ ከ35 በላይ  ህጻናትን አቅፎ የመጀመሪያው ፕሮጀክት አዳማ ላይ በመልካም እንቅስቃሴ ላይ ይገኛል። አላማዉም በተለያዩ የኢትዮጵያ ከተሞች ላይ ሴንተሮችን በማቋቋምና ወጣቶችን ወደማዕከሉ እንዲመጡና ከአልባሌ ቦታ እንዲቀሩ በማድረግ ወደፊት መሆን ለሚፈልጉት አላማ ማገዝና መክሊታቸውን እንዲያገኙ ፡ በትምህርት ፡ ከተለያዮ አለማት ሰዎች በመጋበዝ የልምድ ልዉውጥ እንዲያደርጉ እድል ማመቻቸት ነው። በዚ አጋጣሚ “ድር ቢያብር አንበሳ ያስር” ነውና የሁሉም ሰው እገዛ ያስፈልገናል:: እናም በሶሻል ሚድያ ማለትም በዌብሳይታችን በFacebook, **በ**instagram, በ Telegram ወዘተ  "SunEko Ethiopia" በሎ በመፈለግ የሰኒኮ ቤተሰብ ይሆኑ ዘንድ ጥሪዬን አቀርባለሁ። አመሰግናለሁ!!

**ቀንዲል**፡-እኛም የአውደ ብሩሀን ገጽ ግዜህን እጣበህ እንግዳችን ስለሆንክ በቀንዲል መጽሄት እና አንባቢያን ስም ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

ቀንዲል

CONTACT US
0912178520
0920019699

በናሆም ሸዋንግዛው
( ShewangizawNa-hom@gmail.com)

# አድዋና ወጣቱ

የኢትዮጵያውያን የአንድነት ተምሳሌት የአይቻልምን አስተሳሰብ መስበሪያ ቀንበር፤ የጥቁር ህዝቦች የነፃነት ተጋድሎ መነሻ "አድዋ"!። ክብርና ምስጋና የነፃነት ሳይሆን የድል ቀን በደማቸው አዋጅተው ላኖሩልን ቀደምት አባቶቻችን ይሁን። በአድዋ ጦርነት ላይ ከታዳጊ ( በ ፲፫ አመታቸው የዘመቱትን ተክለሃዋሪያት ተክለማሪያምን ጨምሮ) - ወጣት - አዛውንት ጦር ፤ በበሳል አባት አመራሮች እንደ ፊትአውራሪ ዲነግዴ፣ ባልቻ አባነፍሶ ፊትአውራሪ ገበየሁ ..... እና እምዬ ምኒልክ፤ እንደ እቴጌ ጣይቱ አይነት በበሳል አመራር እና ማስተባበር የተካኑ እናት አመራሮች እየተመራ ያ የወቅቱ ትንታግ ትውልድ ወቅቱን ያዋጀ የሁላችን በሁላችን ደም የተፃፈ ደማቅ ድልን አጎናጽፈውን አልፈዋል። እኚህ ጀግኖች አርበኞች በዘመኑ የተስፋፊነት አላማን ያነገበውን የቀኝ ግዥ የጥልያን ጦር ላይ አንጸባራቂ ድል ተጎናፅፈዋል። ደማቅና ጉልህ የታሪክ ክፍል አትርፈውልን አልፈዋል። ... እኛ ስ?.... አርበኝነት እንደየዘመኑ በዘመኑ ፈሊጥ ይቃኛል። በዚህ ዘመን ጦር ሰብቆ መዋጋት የዘመኑ የቴክኖሎጂ ዝማኔንና የችግሮቻችን አይነት አይዋጅም።አርበኝነት በኛ ዘመን እርሀብን፣ ድርቅን፣ እጦትን፣ ጥላቻን፣መቃቃርን፣ መለያየትን፣ ድህነትን፣ ማህይምነትንና ጭቆናን ነው።በስሜት ማዓበል እንደ ቅቤ ከመናጥ፣ እንደ ጎሽ መንጋ ከመነዳት (የሚከፋው በኢ- ሃሳባዊያን) ከመነዳት በመቆጠብ ሰከን ብለን "የረጋ ብዙ ይወጣዋል እንዲሉ አበው" በችግሮቻችን ዙሪያ እየመከርን መፍትሄ በማበጀት የችግሮቻችንን ግብዓተ-መሬት ለማስፈፀም መታተር ነው። በኛ ዘመን በምግብ እጦት በርሃብ አለንጋ እየተጋረፉ ነፍሳቸውን የሚያጡትን ካለመታደግ የባሰ ውድቀት ከቶ ከየት አለ?... ።
የአገሬ ከብት ማለቅ፣ የሰውን መውደቅ አይቼ እስካሁን ዝም ብያለው።...እንደፍልፈል መሬት ይቆፍር ጀመር። አሁን ግን በፈጣሪ ረዳትነት አገሬን አሳልፌ አልሰጠውም።
.....ጉልበት ያለህ በጉልበትህ እርዳኝ ጉልበት የሌለህ ለልጅህ፣ ለምሽትህ፣ ለሀይማኖትህ ስትል እርዳኝ። ወስልተህ የቀረህ እንደሆነ ግን ኋላ ትጣላኛለህ።አልምርህም። (አፄ ምኒልክ ለአድዋ ጦርነት ያስለፈፉት አዋጅ)።
ታዲያ እምዬ ምኒልክ ለሃገር፣ ለሃይማኖት፣ ለልጅና ለምሽት ፍቅር እስከ ጦር ሜዳ መጥቶ ተዋግቶ ሀገሩን ነጻ ያወጣ ነው የለመኑት።...እኛስ ምን እንማር?.... ታማኝነት፣ አርበኝነት፣ ክብር፣ ፍቅር፣ መተባበር፣ ችግርን መፍታት(አገር-አድን)፣ እምነት፣ መስዋዕትነት በሰፊው መቅሰም እንችላለን።
በድል ጎዳና ለመጓዝ ከዚህ አዋጁን ተከትሎ ከተመመው፤ ወደ ጦር አውድማው ዘምቶ አንፀባራቂ ድል ካስመዘገበው ትንታግ ትውልድ ብዙ መማር አንችልምን?።

....እኛ እኮ.....መሞት በጦር ሜዳ መዋደቅ ሳይጠበቅብን በቀላሉ ከገፀ-ድሩ ወከባ ሰከን በማለት፣ በማመዛዘን፣ እንዴት....ለምን....መቼ...የት....የሚሉትን መጠየቂያዎች በመጠቀም በመሞገት፤ ከምንም በላይ የድርሻችንን በመወጣት ( ተማሪው ትምህርቱን በደንብ በመከታተል፣ በስራ ላይ የተሰማራው ስራውን ሳይንቅ ሳያቀል በመከወንና ማህበራዊ እሴቶቻችንን በመጠበቅ በመተግበር) እንዲሁም ቀልባችንን ሰብሰብ በማድረግ፤ በቀናኢነት በማሰብ፣ በፍቅር መርህ ለሰብዓዊነት ቦታ ሰጥተን በአንድነት መጓዝ ብቻ....። ባለፈው ለመቆዘም ሳይሆን መጪውን ለመተለም ይረዳን ዘንዳ ታሪካችንን አጥርተን ከስረ መሰረቱ መልካሙን እንደመሰረት ሰንደን፣ ዘመኑን ያዋጀ አርበኞች እንሁን። ይህን ችላ ብንል ያለፈው/ የመጪው አይወቅሰን?......።

ቸር እንሰንብት!!!
ሰላምና ፍቅር ለሀገራችን!!!

# #መዝናኛ



በ ናሁ አስተርአዬ ፅጌ
( nahooasteraye18@gmail.com

የታሪኮች ቋሚ : የነፃነት ማገር
የትስስር ዋልታ : ያቆማትን ሀገር
ውስጥ ውስጧን አጥቅቶ
ዘመም ያደረጋት : የዘመሚት ተግባር
መች ፀንቶ ይቆማል: ሕዝብ በገነባው :የመፋቀር ግምባር!

እሙን ነው
እርግጥ ነው
የመፍረስ ፍርሃት : የመውደቅ ጥርጥር
ባካል ተንሰራፍቶ : እያብረከረከ : የሰውን ልብ ሲያጥር
ጎዳናው መንገዱ : በደም የታተተው
መሞትን ሲያዘክር : ለተመለከተው

ዓመቱ ሲሞላ : ቀን እየጎደለም
በተስፋ መቆየት : የምኞትን ያህል : የሚቀልል አይደለም!

እርግጥ ነው
እሙን ነው
ኗሪ በየነጋው : እንደዛፍ ሲጋደም
ኃሴት ዘበት ሆኖ
የዜጎች ህላዌ : በኃዘን ተወጥኖ : በኃዘን ሲደመደም
የቃየሎች ድንጋይ : በአቤሎች ማጅራት: ሰርክ ሲወረወር
የነሙሴ መንጋ : በፈርዖኖች መንገድ : በግድ ሲዘወር
አይመስልም የሚቻል : በበትር ሰንጥቆ : ባሕሩን መሻገር
ግብጽ ላይ ተቀምጦ : የሚያልም አንድ የለም:የተስፋይቱን ሀገር!!

እርግጥ ነው
እሙን ነው
ቤቱን የደገፈ : የታመንንበት አምድ : ምስጥ ሲወጥቀው
የጠናውን ቋሚ : ዘመሚት ነቅንቆ : ኗሪን ሲያስጨንቀው
ዛሬን እየሞቱ : ነገን መኖር ማለም
የማሰብን ያህል
የማውራትን ያህል : የሚቀልል አይደለም!

እናም . . . . . .
በጋን ተደብቀን : ላለም እንዳንበራ
ከል ሲሆንብን : የእውርነት ጉዞ : የታሪክ ድንበራ
ጀንበር እየቆጠርን : ዘመን እያደስን
ባረጀ አስተሳሰብ : አዲስ እያሰስን
ታሪካችን ሳይወርድ : ከአህያ ጀርባ ላይ : ከፈረሶች ጫንቃ
ፊቷን አዞራብን : ዓለማችን ንቃ
በጋራችን ምድር : በግል ተቸግረን : ተብለን ኋላቀር
ዘመሚት ከዘመን : ዘመም እያረገን
ለምን ነው የምንቀር!??

እግር ተወርች የሚያስር
የዘር አስተሳሰብ : የመንጋዎች ፍና
በዕልፍ የሚያከስር
የዘውጌዎች ጉዞ : የጎጥ ፍልስፍና
ሁሉን የወከለን
ሁሉን ያማከለን
የሀገር ደጋፊ : መቆሚያ ምሰሶ
እንዳረጀ ዋርካ : ሊጥለው ገርስሶ
እየጣረ እያየን
ድማሬን መንነን : ልክ እንዳሻራችን :ምነው ተለያየን!??

**#መዝናኛ**

ግድየለም እንመን
ግድየለም እንታትር
እንደመር እንጂ : በጎሳ በክልል : ሕይወትን አንከትር
ለዘበት አይልቅም : የፈርዖኖች ብርታት : ከሙሴያችን በትር!
እንኑር ለዋልታው
ለምሰሶው እንቁም
ይበቃል ቾልታው
እንኳንስ ተፋዝዘን: ሳንወጣና ሳንወርድ: ምስጦች አይጠቁም!

ግድ ይስጠን ለሀገር : ለሰፈ ቤታችን
ለኢትዮጵያ ይጭነቀን : ለውብ ርስታችን
ታዲያ በዚህ ሁሉ
ሀገር አንቋረስ : ድንበር አናበጃጅ
ሀሳብን የሚያጥር : ክልል አናዘጋጅ
ድል ስሙር አይሆንም
በትግል በልፊያ
በሽምያ በግፊያ
በምልልስ ሩጫ : በመኳነን ጥድፊያ
ድማሬ ነው ጠበል : የዘመሚት ማጥፊያ!!

✍✍✍
(ዘመሚት -- ቀላ ያለ አደገኛ )ምስጥ



በያብስራ ካሳ

# ከፈጣሪ በታች ያለ ፈጣሪ

ከኖሩ አይቀር አለማሰብ አይቻልም። ሳያሥቡም መናገር ያዳግታል። ሳያስቡ ሳይናገሩ መስራት ደሞ ጭራሽ የማይታለም ነው። እንደመታደልም ቆጠርነው እንዳለመታደል ይህቺ የምንኖርበት አለም በብዙ ሚሊየሞች ውስጥ ሺምንተሺ ዳናዎች ሲመላለሱ ገንብተው ከውጥንታ ያሳለፏት ለፍፃሜ ያልበቃች የርክብክብ ቤታችን ነች። በአጭሩ አለማችን ማለት የደረስንባት ሁላ ያሻንን እየቀጠልን ያላሻንን እየቆረጥን የምናሽሞነሙናት የውርስ ጌጣችን ናት ማለት ይቻላል። ታድያ በዚህ ሁላ እልፍ ዘመን ውስጥ አለም አእላፍ ገንቢዎቿ እና አዕላፍ ናጂዎቿ ሲገነቡ ለመካብያ ሲያፈርሷትም ለመናጃ የሚጠቀሙበት ገናና መሳርያቸው ሃሳብ እንደሆን ልብ ይበል:: ምክንያቱ ደሞ በአለም ላይ ያለሃሳብ የተገነባ ያለሀሣብም የሚፈርስ ነገር የለምና ። ያለሀሳብ የተገነባ ነገርም አይገኝም።
ሰማይና ምድር እንኳ ሳይቀር በቃል ከመወለዳቸው በፊት የሃሳብ ፅንሶች ነበሩና። ምድራችንን በምህዋሯ እና በዛብያዋ ከሚያዞራት እና ከሚያሽከረክራት ሀይል ባልተናነሰ አለማችንን እያሌ ሀሳቦች ወዳሻቸው እንደእንዝርት እያሾሩ እንዳሻቸው ነድተዋታል ወደ ፊትም ይነድዋታል።

እዚህ ጋር አንድ ማጣቀሻ ላምጣ ደራሲ ጋሽ ስብሀት ገ/እግዚሐብሄር ማስታወሻ ተሰኝቶ በደራሲ ዘነበ ወላ በተፃፈው የህይወት ታሪኩ በኩል ያለንበትን ዘመን ስላነፁት ሶስት ታላላቅ ሰዎች እና ሀሳባቸው ይነግረናል:: ጋሽ ስብሀት እንዲህ ብሎ ይጀምራል "ያለንበት ዘመን የሶስት ሰዎች መዋጮ ነው :: ኣልበርት ኢንስታይን ካርል ማርክስ እና ሲግሞንድ ፍሮይድ ናቸው::" የመጀመሪያው እውቁ የፊዚክስ ሊቅ አልበርት ኢንስታይንና በሳይንቲስቱ በኩል የተገኙት ሀሳቦች መካከል አሁን የአለም ሀያል የሚባሉት ሀገራት ሀያልነት ያስናኘ እና አለኝ ብለው የሚፎካከሩበት እና የሚመኩበትን የኒኩልየር ሀሳብ ማየት ይቻላል:: የኒኩልየር መሳርያ ነገር አለምን ከሚያስጨንቁዋት ዋና ዋና ጉዳዮች ውስጥ ዋነኛውን ቦታ ይወስዳል ብንል ማጋነን እንደማይሆን ተስፋ አደርጋለው።

በዚህ ሃሳብ ጦስም አለም ከቅርብ አመታቶች በፊት ባስተናገደቻቸው የጎራ ጦርነቶች ውስጥ በሄሮሺማ እና ናጋሳኪ ላይ የደረሰው ጥቃት በደማቁ የታተመ ጥቁር የመተላለቅ ጠባሳ አርገን መውሰድ እንችላለን:: የአልበርት ፅንሰ ሃሳቦች እንደገቡበት እጅ ላእለም እንደጡብም እንደ ሽብልቅም ሆነው ሲገነቡዋትና ሲያፈርስዋት ኖረዋል። ሌላው ያለንበትን ዘመን ሰሩ ከተባሉት ሰዎች አንዱ ደሞ ይሁዲው ፈላስፋ ካርል ማርከስ እናገኛለን:: እዚህ ጋር ጋሽ ስብሃት የማርከስ ትንቢት አለምን ለሁለት በካፒታሊዝም እና ሶሻሊዝም እንደገመሳት ይነግረናል:: የካርል ማርክስ ፅሑፎች በገንዘብ( ኢኮኖሚ) እና የኅይል ፖለቲካ ላይ ያተኮሩ ነበር። በማርክስ አስተሳሰብ ደመወዝ ተከፋይ ጉልበት ባለበት ሁሉ የመደብ ትግል ይኖራል ብሎ ያምን ነበር። በእርሱ እመነት ይህ የመደብ ትግል በሰራተኞች አሸናፊነትና የበላይነት የሚደመደም ነው።

"…..ሰዎች ጠላታቸው በልባቸው የተቀመጠው እኩይ ሀሳብ ነው…."

በሌላ ጎን ካርል ማርክስ ከደረሳቸው መጻሕፍት ዳስ ካፒታል የሚሰኘው እንደ ዋና ስራው ተደርጎ ይወሰዳል። ዳስ ካፒታል እንዴት ካፒታሊዝም እንደሚሰራ ሲገልጽ በዚያው ልክ ካፒታሊዝም የሚፈጥራቸውን ችግሮች አብሮ ያብራራል። የማርክስ ርዕዮተ አለም ለሶሻሊዝም መነሳትና ለሩሲያ አብዮት መንስኤ እንደሆነ በብዙዎች የታመነ ነው። ሌላው ሶስተኛ ሰው ድሞ ታላቁ የስነ ልቦና ተመራማሪ ሲግመንድ ፍሮይድ ነው።ይህ ሰው በማጠቀሻችን ላይ እንዲህ ሲባል ይሞካሻል። " ፍሮይድ ፍተሻ ነው ያደረገው። እነ ኮሎምበስ እነ ማርክ ፖሎ ባህር ለባህር እና የብስ ለየብስ አሰሱ። ኒል ኣልመስትሮንግ ወደ ጨረቃ ወጣ ፍሮይድ ግን ወደ ወስጡ ነው የጠለቀው። ከእርሱ በፊት ደፍሮ የገባ የለም። " አለም ስለ ስነልቦና ያላትን አመለካከት በሀሳቦቹ እና በምርምሮቹ የቀየረው ፍሮይድ የስነ ልቦናን ዘርፍ ወደ ላቀ ደርጃ በማድረስ ለእያሌ ችግሮች መፍትሄ አበጅቶዋል። ከዚህ ተነስተን ታድያ በስነ ልቦና ረገድ የፍሮይድ ሀሳቦች አለምን ገምብተዋታል ብንል አላጋነንነውም።

ታድያ የሶስቱም ሃሳብ ኣለምን በተለያየ ኣቅጣጫ ገምብተዋልም አፍርሰዋልም። አንዳንዴ ከመነሻው አሉታ ያልነበረ ሀሳብ ሁለተኛ ሶስተኛ እጅ ላይ ሲደርስ ወይ ሌላ ሀሳብ ጋር የመቀላቀል እድል ይኖረዋል። ታድያ ያኔ ወይ ይበልጥ አውንታ ይሆናል አልያ ደሞ ብሶበት ሌላ መስመር ይዞ አሉታዊ ሆኖ እናገኘዋለን። የትም እንሂድ ብቻ ያለሀሳብ የሆነ የሚሆንም የለም። እኛም ሰዎች ብንሆን ከአፈርነታችን በፊት ሀሳብ ነበርን እኮ! ከዛን ነው ከእኛው ሀሳብ ደሞ አኳኃናችን አረማመዳችን አበላላችን አተኛኘታችን ማንነታችን አኗኗራችን የሚቀረፀው።

ድንቅም አደል! ይሄንን ሁላ ነገር ሀሳብ በሚባል ቅንጣት መፈጠሩ? እያንዳንድዋ በየደቂቃው የምናስባት ሀሳብ ታውቆንም ይሁን ሳይታወቀን በኛ ማንነት ላይ ተፅዕኖ ማኖሯ ? ወዲህ ደሞ የሰው ልጅ አይምሮ በቀን ከ50,000 ያላነሱ ሀሳቦችን እንደሚያስብ ሳይንስ ተናግሮ አጀብ አስብሎን ካበቃ በኋላ እየተጠቀምንበት ያለው ግን አስር ፐርሰንቱን ብቻ እንደሆን ይለጥቅልናል። ይህም ሌላ አጃዒብ ነው። እኛ ደሞ ከሱ ለጥቀን እንዲህ ራሳችንን እንጠይቅ " በቀን ከምናስባቸው እያሌ ሀሳቦች ውስጥ ምን ያህሉ ናቸው ገንቢ? ምን ያህሉስ አፍራሽ ናቸው? ስለ ሰዎች ስናወራ የሰዎች ወዳጅ እና ጠላት በታሰበው ሰው ውስጥ ስላነሱ ያለው በጎ ወይም መትፎ ሀሳብ ነው።

#እጃኢብ

በአለም ላይ ክፉ የምንላቸው ሰዎች ጠላታቸው በልባቸው የተቀመጠው እኩይ ሀሳብ ነው። በጎ የምንላቸው ሰዎች ወዳጃችን ደሞ ሰናይ ሀሳባቸው ሆኖ እናገኘዋለን። በሚያስቡት በኩል እነሱነታቸው ይጨብጠናል። ጨብጠን እናበቅም ስብዕናችውን ሰፍረን እንመዝናለን።
ሀሳብ ከመፀነሱ ለጥቆ በሁለት ነገር ሊወለድ ይችላል :: በቃል ወይም በተግባር :: ይህን ለማብራራት ሀሳብን በዘር ልንመስለው እንችላለን:: ዘሩ አጎንቁሎ ሲበቅል ቅርንጫፍም ሲያወጣ ዛፍ ተብሎ ይጠራል:: ዛፍ ብቻም ሆኖ አይቀርም ውሎ አድሮ ደሞ በቅርንጫፎቹ ማህፀንነት መሳይ ፍሬዎቹን መውለድ ይጀምራል:: ፍረዎቹም እንደገና ዘር ተብለው ካፈር ተቀብረው አፈር በልተው ቀና ብለው ሽቅብ ተንጠራርተው ሰማይ ሲጠቅሱ መልሰው ዛፍ ይባላሉ:: ታድያ አሁን ዛፍ ብቻ አደለም ዛፎች ደረጃ ተደርሰዋል:: ታድያ እኚህ ዛፎች የህይወት ዛፍ ከሆኑ ዛፎቹን እየተንከባከቡ ህይወትን ማስቀጠል ይገባል:: በሌላ ፅንፍ ደሞ ዛፎቹ ክፉ የሞት ዛፎች ከሆኑ ዛፎቹን መቁረጥ ግድ ይላል:: ታድያ ዛፎቹ ሲቆረጡ ቆራጩ ዛፉን ዘሎ ከስር ግንዱ ልመንግለው ካለ ዛፉን ቢቆርጠውም መልሶ በዝቶ እንድያቆጠቁጥ እየረዳው መሆኑን ልብ ይባል:: ምክንያቱም ዛፎቹ በየቅርጫፎቻቸው ላይ ያንጠለጠሉት ፍሬዎች መርገፋቸው ኣይቀሬ ነውና::

በዚህ ኣለም ወንጀል እና ወንጀለኛ የበዛው ከሃሳቡ ይልቅ ወንጀለኛውን በማሳደድ ሰፊውን ጊዜያችንን ስለምንጨርሰው ይመስለኛል :: ስንቶች ናቸው ታርመዋል ተብለው ታርመናል ብለው ወደድሮው ማንነታቸው ተመልሰው ውሃ ሚወቅጡት?

ክፉዎችን ከክፋታቸው ለመከላከል ሀሳቡ ሚጎርፍበትን ምንጮች ፈልጎ ማጥፋት ግድ ይለናል:: ለምሳሌ አንድ ከባድ ወንጀለኛ በሞት ቅጣት ተቀጣ አልን:: (ትልቁ ዛፍ ተቆርጦ ወደቀ) ከዛ ጥቂት ቆይተን ብዙ የእሱ አይነት ወንጀለኞች ፈልተው እናገኛለን:: ምክንያቱም ስለ ፍሬዎቹ ምንም ያሰብነው ነገር ስላልነበር እሱ ወደቀ እነሱ ረገፉ :: እሱ ደረቀ እነሱ ፀደቁ ::

እናም እላልሁኝ ሳይታሰብ የተገነባም ሳይታሰብም የሚፈርስ ነገር የለም :: አበቃሁ!

ቀንዲል
DIGITAL MAGAZINE

SEARCH @KendilM ON TELEGRAM
Contact Us 0912178520
0920019699



በ ፍራኦል መስፍን
( በመቀለ ዩኒቨርሲቲ
ጤና ሳይንስ ኮሌጅ
ሌክቸረር እና ሀኪም )
( fraolmesfin8@gmail.com)



# የ2030

## 3ተኛው የአለማችን ገዳይ በሽታ

ብዙ ሰዎች" የአዕምሮ ጉንፋን ወይም "The common cold of mind" እያሉ ይጠሩታል።እንደ ዓለም አቀፉ የ ጤና ድርጅት ትንበያ ከሆነ እንደ አውሮፖውያን አቆጣጠር በ 2030 3ኛው በዓለማችን ሰዎች የሚሞቱበት ምክንያት ይሆናል ።

### ድባቴ (Depression)

### ድባቴ (Depression) ምንድነው?

ሰው ሆኖ የሀዘን ስሜት የማያጋጥመው የለም። የሀዘን ስሜቱ ግን ጊዜያዊና ዕድሜው ከቀናት ያልበለጠ ነው፡፡ ሆኖም አንድ ሰው ከገባበት ሀዘን በቶሎ መላቀቅ ካልተቻለ የድባቴ ህመም አጋጥሞታል ማለት ይቻላል፡፡ የድባቴ ህመም ውስጥ ያለ ሰው ደግሞ ከራሱ አልፎ በዙሪያው ያሉትን ሰዎች ዕለታዊ የህይወት እንቅስቃሴ ያውካል፡፡ የድባቴ ህመም በብዙ ሰዎች ላይ የሚከሰት፤ ችላ ከተባለ ግን የአዕምሮ ጤናን የሚያውክ አደገኛ በሽታ ነው፡፡

### የድባቴ ምልክቶች ምንድን ናቸው?

የድባቴ ምልክቶች በሁሉም ሰው ላይ ተመሳሳይ ላይሆኑ ይችላሉ፡፡ የህመሙ ደረጃ፣ቆይታና አስከፊነት እንደየግለሰቡ የድባቴ ሁኔታ ይለያያል፡፡ ሆኖም ቀጥሎ ከተዘረዘሩት በርከት ያለው ካጋጠመ ድባቴ መኖሩን ይጠቁማል፡፡

ተከታታይ የሆነ የሃዘን፣ የንዴት፣ የብስጭት፣ የቁጣና የባዶነት ስሜት

የተስፋ ማጣትና ጨለምተኝነት አመለካከት ራስን መውቀስ፣ዋጋቢስና ረዳት የለሽ የመሆን ስሜት

በትንሽ በትልቁ መበሳጨትና ቅብጥብጥነት ለወትሮው በፍቅር ለምናከናውናቸው እንደ ስራ፣ጨዋታ፣መዝናናት እና ወሲብ ለመሳሰሉት ፍላጎት ማጣት

ድካም እና ተነሳሽነት ማጣት

አትኩሮት ማጣት፣ ዝንጉነትና፣ ወሳኔ ለመስጠት መቸገር

መጫጫን፣ የእንቅልፍ መዛባት (እንቅልፍ ማጣት ወይም ለረዥም ጊዜ መተኛት)

ከመጠን ያለፈ መመገብ ወይም የምግብ ፍላጎት መቀነስ ራስን ማጥፋት መፈለግና መሞከር

በህክምና መታገስ ያልቻለ ራስ ምታት፣ቁርጠት፣ ቁርጥማትና የምግብ አለመፈጨት ችግር

### የድባቴ ዓይነቶች ምን ምን ናቸው?

ከባድ የድባቴ ህመም:- ማንኛውም ሰው በህይወት ዘመኑ አንድ አይነት የድባቴ ምልክት ሊታይበት ይችላል፡፡ ሆኖም አንድ ሰው ላይ የተለያዩ የድባቴ ምልክቶች አዘውትረው ማጥናት፣ ስራ መስራት፣ መተኛት፣ መዝናናት የመሳሰሉት ዕለታዊ እንቅስቃሴዎቹን የሚያውክበት ከሆነ ከባድ የመደበት ስሜት ውስጥ ነው ማለት ይቻላል፡፡

2. የተራዘመ የድባቴ ህመም:- የተራዘመ የድባቴ ስሜት ለሁለት ዓመትና ከዚያ በላይ ለሆነ ጊዜ የሚቆይ የመደበት ምልክቶች ይታይበታል። የተራዘመ ድባቴ እለታዊ ተግባርን ሙሉ በሙሉ አያውክም፡፡ ሆኖም ሰዎች መልካም መንፈስ እንዳይኖራቸውና መደበኛ ተግባራቸውን በሚጠበቀው ደረጃ እንዳይፈፅሙ ያደርጋል፡፡

3. አነስተኛ የድባቴ ህመም:- አነስተኛ የድባቴ ስሜት ምልክቶች ለሁለት ሳምንታት ወይም ከዚያ በላይ ይቆያሉ፡፡ አነስተኛ የመደበት ስሜት ከጅምሩ ህክምና ካልተደረገበት ስሜቱ ቀስ በቀስ ወደ ከፍተኛ ድባቴ ሊቀየር ይችላል፡፡

4. ሳይኮቲክ ድባቴ:- ሳይኮቲክ ድባቴ ከፍተኛ ደረጃ ላይ በደረሰ የድባቴ ህመም የሚመጣ የአዕምሮ መቃወስ ነው፡፡ ሳይኮቲክ ድባቴ ያለበት ግለሰብ በተሳሳተ ግምት ይረበሻል፡፡ ከእውነታ ጋር የሚጋጭ አስተሳሰብ ያራምዳል። በተጨማሪም ለጤናማ ሰው በማይሰማ እና በማይታይ ሀሳብ የመንፈስ ጭንቀት ይደርስበታል፡፡

5. ድህረ ወሊድ ድባቴ:- ይህ የድባቴ ዓይነት ከወሊድ በኋላ በሚከሰት የአካልና የአኗኗር ዘይቤ ለውጥ ጋር ተዛምዶ በአንዳንድ እናቶች ላይ የሚያጋጥም ነው፡፡

### የድባቴ መንስኤዎች ምንድን ናቸው?

የድባቴ ህመም መንስኤ ይሄ ነው ብሎ በእርግጠኝነት ለመናገር ያዳግታል፡፡ ሆኖም የመስኩ ተመራማሪዎች ለድባቴ ህመም የሚያጋልጡ ሁኔታዎችን እንደሚከተለው ይዘረዝሯቸዋል፡፡

- በዘር የመጣ ከሆነ
- አዕምሮን የሚረብሽ ከባድ የህይወት አጋጣሚ
- የሚወዱት ሰው በሞት መለየት
- ከሰዎች ጋር ያለ ሠላማዊ ግንኙነት መናጋት
- አዕምሮ ሊሸከመው ከሚችለው በላይ የሆነ ሀሳብና ሁኔታ ሲገጥም

በተጨማሪም ኤችአይቪ በደማቸው የሚገኝ ሰዎች በቫይረሱ ምክንያት በሚከሰት የአእምሮ ጉዳት፣ ጭንቀት፣ መገለልና የሞራል ውድቀት ምክንያት ለድባቴ ከሌላው ይበልጥ ተጋላጭ ናቸው።



## ድባቴን እንዴት መቆጣጠር ይቻላል?

የሚከተሉትን ጤናማ የአኗኗር መንገዶች በመከተል ድባቴ ሳይባባስ ማቆም ይቻላል።


- የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ማድረግ
- ጤናማ የአመጋገብ ስርዓት መመስረት
- ከአልኮል፣ከትምባሆ እና ከአደንዛዥ ፅፆች መቆጠብ
- አሉታዊ ሀሳቦችን ከአዕምሮ አስወግዶ አዎንታዊ ጎኖችን ማሰብ መለማመድ
- በህይወት ውስጥ ለችግሮች ፍፁም የሆነ መፍትሄ እንደሌለ ማስታወስ
- የሚያጋጥሙ ፈተናዎችን ለማለፍ በትዕግስት ጠንክሮ መስራት
- ለሳቅ ለጨዋታ በአጠቃለይ ለመዝናኛ ጊዜ ማበጀት
- ለሰዎች በጎ ነገር በማድረግ መልካም ወዳጅነት ማፍራት
- ጭንቀትና ስጋትን ለቅርብ ሰው ማካፈል



አንድ ሰው የድባቴ ስሜት ሲሰማው ከላይ የተዘረዘሩትን ሞክሮ መሻሻል ካላሳየ ህክምና በወቅቱ መጀመር ይገባዋል። የድባቴ ህመም ያጋጠመው ሰው መድሀኒቱን በአግባቡ ከተከታተለና ተገቢውን ህክምና ከባለሞያዎች ካገኘ ምርታማ እና ለሚኖርበት ማህበረሰብ ትርጉም ያለው አስተዋፅኦ ማድረግ ይችላል። ህክምና ካላገኘ ግን ምልክቶቹም እየጨመሩና ህመሙም እየተባባሰ ይመጣል። ህክምናው ውጤታማ እንዲሆን ደግሞ ሰዎች ሀሳቦቻቸውንና ጭንቀቶቻቸውን ከሀኪሞቻቸው ጋራ በግልፅ መነጋገር ግድ ይላቸዋል።

ህክምና የሚያስፈልገው መቼ ነው?

አንድ ሰው የድባቴ ስሜት በዕለት ተዕለት ጤናማ አኗኗሩ ላይ እክል የሚፈጥር ከሆነ የህክምና እገዛ ያስፈልገዋል። በተለይም ታማሚው ራሱንም ሆነ ሌሎችን የመጉዳት አዝማሚያ ካሳየ በአቅራቢያ ወደሚገኝ ማንኛውም የጤና ተቋም ዘንድ ሄዶ የመድሀኒት ወይም የሌላ ህክምና አገልግሎት እንዲያገኝ ሊረዳ ይገባል።



በ ዞስ ካለስ
( Zoskales27@gmail.com)

# የፊዚክስ ምሁራን ዩኒቨርስ በዚህ ያህል ፍጥነት የሚሰፋበትን ምክንያት አለማወቃቸው፣ አዲስ የፊክዚክስ ቀመር አስፈልጓቸው ይሆን?

ዝየጭለማው ሀይል(dark energy) ምንድነው? ብላክ ሆል(black hole) ማለትስ? የአንድ ግዙፍ ኮከብ ግብዓተ መሬት ሱፐር ኖቫን ሲፈጥር ከሚከሰቱት ነገሮች ውስጥ አንዱ ወደ ኒዎትሮን ኮከብ መለወጥ እንደሆነ ይታወቃል፣ ነገር ግን አንዳንድ ግዙፍ ክዋክብት ኒዎትሮን ኮከብ ሆነው ብቻ መቆየት ይሳናቸዋል፣ በሂደቱም ኒውትሮን ኮከብ ራሱ ብትንትኑ ወጥቶ በመሀሉ አይቆጠሬ የሆነ ግራቪቲ ያለው ጥቁር ነጥብ ሚፈጥር ሲሆን ይህም ብላክ ሆል ይባላል። ብላክ ሆል ከስበቱ ኃይለኝነት የተነሳ አንድ ክብደት ያለው ቁስ አካል ቀርቶ ብርሀን እንኳ በአጠገቡ ቢያልፍ ውጦ የሚያስቀር እጅግ አደገኛና አስፈሪ ቦታ ነው። ብርሀንን ውጦ ሚየስቀር ልዩ ቦታ ለመጀመሪየ ግዜ ያገኙት በ18ኛው ክፍለ ዘመን ጆን ሚቼልና ሲሞን ላፕሌስ ሚባሉ ልኢቃን ሲሆኑ፣ አጠቃላይ ስለ ብላክ ሆል ሚገልፀው ሬላቲቪቲ ትንተና ይፋ የሆነው ደግሞ 1916 ካርል በሚባል ሰው ነው። በ1967 የኒዎትሮን መገኘት ስለ ብላክ ሆል በተወሰነ መልኩም ቢሆን የተሟላ አውቀት እንዲኖራቸው ረድቷቸዋል።

ትላልቅ ብላክ ሆሎች አይደለም መሬት፣ ጁፒተርና ፀሀይን አለፍ ሲልም ሙሉ ዩኒቨርስን ውጦ ማስቀረት ሚችል አቅም አላቸው፣ ጥብስቁ የብላክ ሆል ማስ ነው እንጂ ግዙፍ በይዘት ከትንሽ ነጥብነት አያልፍም። የብላክ ሆል ክልል ውስጥ ምንም ማምላጥ ማይቻልበት ዝግ የሆነ ቦታ ኢቬንት ሆራይዘንም ይባላል( event horison)፣ ማንኛውም ነገር ይሄን ቦታ አልፎ ሚገባ ከሆነ ለአንዴና ለመጨረሻ ግዜ ገብቶ ይቀራል፣ መመለሻ የለውም፣ ለምስሌ አንድ የጠፈር ተመራማሪ በመንኮራኩር እየሄደ ኢቨንት ሆራይዘነን ሚየልፍ ከሆነ አስቂኝ አጠፋፋ ነው ሚጠፋው፣ መንኮራኩሯም ሆነች ሰውዬ ወደ ትናንሽ አተሞች በመሰባበር እስከመጨረሻው ላይመለሱ ስልቅጥ አድርጎ ይውጣቸዋል። አስቸጋሪው ነገር ብላክ ሆሎች ያሉበትን ቦታ ለማወቅ በጣም ከባድ ሲሆን፣ ማወቅ ያስቸግራል። ስሙም እንደሚለው ጥቁር ነጥብ ስለሆኑ፣ በዙሪያቸው በሚዞሩት ብርሀናማ አካላት ምክንያት፣ በሚፈጠር ነፀብራቅ ብቻ ነው ልናውቅ ምንችለው፣።

ብዙ በዙሪየው ተካታዮች ያሉት ብላክ ሆል፣ ትላልቅ ኮኮቦች፣ ሳታይላይቶቹ፣ ፕላኔቶችንና ኔቡላዎችን በዙሪያው እያስከተለ ተከቦ ይኖራል፣ ቀን ጥሏቸው ኢቨንት ሆሪይዘንን የለፉት ደግሞ በብላክ ሆል ተውጠው ይቀራሉ።

ሳይንስ እንደደረሰበት ከሆነ ይህ ሁሉ ክዋክብት፣ ፕላኔትና የጋላክሲ ክላስተር ሁሉ ቢደመር 4% እንደሆነና ከዛ ውጪ ያለው፣ የዩኒቨርስ አካል ሊታይ፣ ሊዳሰስና ልንረደው በማንችል ሀይልና ቁስ አካል የተሞላ ነው። ይህም ሀይል፣ ጨለማው ሀይል(dark energy) ይባላል። ጨለማ የተባለበትም ምክንያት በምንም መልኩ ልንረዳው ባለመቻላችን የተነሳ ነው፣ እስከሁን ድረስ በቂና አጥጋቢ የሆነ መረጃ አልተገኘለትም፣ እናም ይሄ ጭለማ ሀይል ዩኒቨርሳችን ውስጥ ወደ 70% መጠን ሲኖረው፣ 26% ደግሞ ጨለማና ቁስ አካል( dark matter) በአንድ ላይ በውስጡ ያካተተ ነው።

አሁን በቅርቡ አስትሮኖመሮች ባወጡት ጥናት፣ ከሚገመተው ፍጥነት በላይ ዩኒቨርሳችን እየሰፋች መሆኑን nature astronomy ባወጣው ጥነት ይፋ አድርጓል፣ አጥኚዎቹ እንደሚሉት ከሆነ ለልኬታቸው መሰረት ያደረጉት ትልቁን ብላክ ሆል(suparmassive black hole) እንደ መለኪያነት በመጠቀም ሲሆን እንደ መንደርደሪየነት በውስጡ በሚያመነጨው ረድያሽን ጨረር በብርሀናማ የጋላክሲ አካላት ላይ በሚያሳርፈው ትልቅ ተፅኖ ስሌት በማወቅ ነው። 1600 ሚሆኑ ትላልቅ ብላክ ሆሎች በተወሰደ የጥናት ናሙናዎች መሰረት ዩኒቨርሳችን በጣም እየሰፋ እንደሚገኝና፣ ብላክ ሆልም አንደኛቸው ወደ አንደኛቸው በጣም እየተሳሳቡ እንዳሉ አመልክተዋል፣ ይሄም ከዚህ በፊት ከዩኒቨርስ መስፋት ጋ ተያይዞ ሚነገረውን የተለየ አድርጎታል፣ በቁጥር የተደገፈ አህዳዊ ዳታ ለመግለፅ የሞከሩት እነዚ ምሁራን ካሉበት አቅጣጫ አንፃር የተለያየ ማጠቃላየ ላይ ደርሰዋል፣ ይሄም ልኬቱን ከሚለኩበት ቦታ አንፀር እንደሆነ ይፋ ሆኗል።



ቅርብ ካለው ዩኒቨርስ በስፔስ ቴሌስኮፕ እንደ ሁብልና ጋሂኣ በመሳሰሉት ትልቅ ቴሌስኮፖች ለመለካት እንደተቻለው በማይል 45.6 ፐር ሜጋ ፐር ሰከንድ እንደሚጓዝ መመልከት ተችሏል፣ ይሁንና በርቀት ላይ ሚገኙት ዩኒቨርሶችን መለካት ሚረዳን ፕላንክ በሚባለው ቴሌስኮፕ እንደተለካው 41.6 ማይል ፐር ሜጋ ፐር ሰከንድ መሄዱን ነው አጥኚዎቹ የገለፁት( በነገራችን ላይ 1 ሜጋ ፐር ሰከንድ 3.3 ሚሊዮን የብርሀን ፍጥነት መጓዝ ይችላል) ይሄም ማንንም ማስገረሙ ፣ አያጠያይቅም። ሱፐርኖቫዎች በሚያመነጩት ጨረር በመነሳት የተለካው ይሄ ልኬት ከቢግ ባንግ ቧላ እስከ 4 ወይም 5 ቢሊዮን ያለውን አመት ብቻ ነው ያሳየን፣ ከዛ ቧላስ? እንግሊዝ ከሚገኘው ከዱርሀም ዩኒቨርሲቲና ከጣሊያን ዩኒቨርሲቲ የተወጣጣው ቡድን ውስጥ የተካተቱት ዶ/ር ሉስ እንደሚሉት ከሆነ የጨለማ ውስጥ ሀይል(dark energy) ስበት(gravity) በተቃራኒው መጓዝ እንደምክንያት መቅረብ እንደሚቻል ይገልፃሉ፣ ለዚህም አዲስ ከዳርክ ኢነርጂ አፈትልኮ ሚወጣውን ሀይል ማወቅ ምንችልበት አዲስ የፊዚክስ ፎርሙላ ሳያስፈልግ እንደማይቀርም አመልክተዋል፣ ትክክለኛውን የዩኒቨርስ መስፋት ፍጥነት ወሰን ማወቅ እንደሚክብድና፣ ከቢግባንግ ጀምሮ ዩኒቨርስ የመጣበትን መጠን መኖሩን በብዙ ሰዎች ዘንድ ግንዛቤው እንዳለ ገልፀው፣ ይሁንና ትክክለኛ የሚሰፋበትን መጠን ማወቅ እንዳልተቻለ ግን ጠቁመዋል።




የቀንዲል ዲጂታል መፅሔት የዝግጅት ክፍል መጋቢት 1 ቀን በኢትዮጵያ አየር መንገድ ንብረት በሆነው ቦይንግ 737 ማክስ አውሮፕላን የበረራ ቁጥር 302 ላይ በደረሰው አስደንጋጭ የመከስከስ አደጋ የተሰማንን ጥልቅ ሀዘን እየገለፅን፤ ለሞቱት ወዳጅ ዘመዶች ብርታትን እና መጽናናትን እንመኛለን።

# 250 ሺህ

## በላይ ሰዎችን ይድረሱ!

ምርትና አገልግሎትዎን በ ቀንዲል ዲጂታል መፅሔት በልዩ አቀራረብ ያስተዋውቁ  ከማስታወቂያ የሚገኘው ገቢ በግማሽ ለበጎ አድራጎት ስራ የሚውል ምርት እና አገልግሎቶን እያስተዋወቁ የበጎ አድራጎት ስራ ይስሩ!!

ለበለጠ መረጃ

(+251) 0912178520

(+251) 0920019699

ይደውሉ!

በ ኤርሚያስ ደጀኔ
(ermiyasdejene@gmail.com)



# ተስፋ የቆረጥኩት በተስፋ መቁረጥ ላይ ብቻ ነው!

ስዕል፦ ፅዮሩ መኩንን 0984740577

እንደምን አለህ ጃል?.......ሁሉ ሰላም? የዛሬውን ፅሁፌ መነሻ የሆነኝ ሰሞኑን የምሰማው ተደጋጋሚ እራስን የማጥፋት ሙከራ ነው። እንድያውም ቢደጋገምብኝ እና ነገሩ ግራ ቢያጋባኝ ባልንጀራዬን "ምንድን ነው ነገሩ? ሰዉ ምን እየሆነ ነው እየተነሳ መርዝ የሚጠጣው? እራሱን የሚሰቅለው?" ብለው "ምን ያርጉት ኑሮን ታግለው ታግለው አልሆን ቢላቸውና ተስፋ ሲቆርጡ እኮ ነው" አለኝ። የተስፋ መቁረጥ እጅግ አስከፊነት እና አስቀያሚነት ይበልጡኑ የተረዳሁት ይሄኔ ነው። እናም ይህችን ያነበብኳትን ታሪክ ስለተመቸችኝ ላካፍላችሁ ወደድኩ። መልካም ንባብ!!

በድሮ ግዜ አንድ የፐርሽያ ንጉስ በሶስት ሰዎች ላይ የሞት ፍርድ ፈርዶባቸው የስቅላት ስነስርአቱ ከመፈፀሙ በፊት ለመጨረሻ ጊዜ የሚሉት ነገር ካለ እንዲናገሩ ለእያንዳንዳቸው እድል ሰጣቸው። የመጀመርያዎቹ ሁለቱ ሰዎች ተስፋ በቆረጠ ስሜት ውስጥ ሆነው እያለቀሱ ቤተሰቦቻቸውን ተሰናበቱ:: የሶስተኛው ሰውዬ ተራ ሲደርስ ግን ሰውዬው ንጉሱን አንድ ጥያቄ መጠየቅ እነደሚፈልግ ተናገረ:: ንጉሱም "በል ተናገር!" ብለው ፈቀዱለት። ሰውየውም ንጉሱን "የ ስምንት ወር እድል ከሰጡኝ የሚወዱትን ፈረሶን አሰልጥኜ ክንፍ አብቅሎ እንዲበር ማድረግ እችላለሁ!" ሲል ለንጉሱ ተናገረ። ንጉሱም ደስ እያላቸው "ስምንት ወር ይበዛል ባይሆን ሁለት ወር ልሰጥህ እችላለው። ነገር ግን ፈረሴ በሁለት ወር ውስጥ ክንፍ አብቅሎ መብረር ካልቻለ ተሰቃይተህ እንድትገደል አደርግሀለው!!" አሉት። ሰውየውም በዚህ ተስማማ። ይሄንን የሰሙት አብረውት ስቅላት የተፈረደባቸው ሰዎች "አንተ ሰውዬ መቼስ ፈረስ ክንፍ አውጥቶ እንደማይበር ታውቃለህ። ታድያ ይሄንን እያወቅክ ተሰቃይተህ ለመሞት እንዴት ትስማማለህ?..... ቆይ ምን አስበህ ነው?" ብለው ጮሁበት።

ሰውየውም እንዲህ ሲል መለሰላቸው። "እስቡት እስኪ .....በዚህ ሁለት ወር ውስጥ አራት አማራጮች አሉኝ፡- አንደኛ ማንም ሳይገለኝ ልሞት እችላለው። ሁለተኛ ፈረሱ እራሱ ሊሞት ይችላል። ሶስተኛ ንጉሱም ሊሞት ይችላል። አራተኛ ደግሞ ማን ያውቃል ፈረሱ ክንፍ አውጥቶ መብረር ቢችልስ? አላቸው::

ወዳጄ በምንም ነገር ላይ ተስፋ መቁረጥ የለብንም! አከተመለት ፡ አበቃለት ባልነው ነገር እንኳን አማራጮች እና መንገዶች ስለሚኖሩ እይታዎቻችንን በማስፋት መፍትሄ መፈለግ እንጂ ተስፋ መቁረጥ መፍትሄ አይሆንም። ፈረንጆቹ ሰው የሚሞተው ተስፋ የቆረጠ እለት ነው ይላሉ። እኔም በዚህ ሀሳባቸው እስማማለሁ ሰው የሚሞተው አበቃልኝ፡አማራጭ የለኝም፡ተስፋ የለኝም ያለ እለት ነው። አበቃልኝ ያለ ቀን ያበቃለታል!! አሁን ያለንበት ችግር ለስኬታችን መስፈንጠርያ፤ ለአሸናፊነታችን መንደርደሪያ እንጂ ተስፋ መቁረጫችን ሊሆን አይገባም። ቀስት ስትወረውር አርቀህ ለመወርወር ወደ ኋላ በደንብ እንደምትስበው እና ስትለቀው ሩቅ እንደሚወነጨፍ እንዲሁ ዛሬ ላይ አንተ ወደኋላ ያስቀረህ፡ ከጓደኞችህ ያሳነሰህ ጉዳይ አንተን ወደ ሩቅ ሊያስወነጭፍህ እንጂ ተስፋ ሊያስቆርጥህ አይገባም። ስለዚህ ሁሌም ወደኋላ ስትቀር መወንጨፍ የሚባል አማራጭ እንዳለህ አስታውስ!

ብሩክ የሺጥላ የ'ኔ ስጦታ በሚለው መፅሐፉ ላይ በጣም የወደድኩት ፅሁፍ አለ።(ገፅ 65) እንዲህ ይላል:-
#ዛሬ የገጠመክ ችግር ውስጥ ጣፋጭ ፍሬ አለ።
#ዛሬ ያለህበት መከራ ውስጥ ሕይወትህን የሚቀይር ሀብት አለ።
#ዛሬ ያለህበት ድህነት ውስጥ የነገ ስኬትክና ሀብትህ በህልምህ ውስጥ አለ።
#ዛሬ ያለህበት አሰቃቂ ሁኔታ ውስጥ መንፈስህን የሚያጠነክርና ከትንሹ ወደ ትልቁ የሚያሸጋግር ድልድይ አለ።

#ቅምሻ

ወዳጄ እንኳን አንተ ትል እንኳን መኖሩ የታችኛው የመሬት ክፍል አየር እንዲያገኝ ይጠቅማል!እድሜ ለትንሿ ትኩረት ለማይሰጣት ትል!! የሷ መኖር የታችኛው የመሬት ክፍል አየር አገኘ።
የትል መኖር ለመሬት የታችኛው ክፍል አየር ካስገኘ የአንተ መኖርማ ለስንት ሰው አየር እንደምትሆን ገምት!!
ስለታም ምላጭ ዛፍ አይቆርጥም፡ ጠንካራ መጥረቢያም ፀጉር አይቆርጥም ልክ እንደዚሁ ሁሉም ሰው ለተፈጠረለት አላማ እጅግ አስፈላጊ ነው። እጅግ በጣም አስፈላጊ፡ የራስህ ፋይዳ ያለህ፡ ወሳኝ ሰው ነህ እና የሂወት ትርጉም አትጣ፡ ተስፋ አትቁረጥ፡ አበቃልኝ አትበል!!
ዳዊትን ከማቆም ሰኞን ማቆም ይቀላል እንደሚል ቃሉ ፡ ብራዘር እኔ ደግሞ እልሀለሁ ብታምንም ባታምንም አንተን ከማቆም ሰኞን ማቆም ይቀላል!!
ተስፋ መቁረጥ አያስፈልግም እይታህን አስፋ እና እሩቅ ተወንጨፍ እልሀለሁ።
"ተስፋ የቆረጥኩት ተስፋ በመቁረጥ ላይ ብቻ ነው!" በማለት ለራሳችን ቃል እንግባ!!

ቸር እንሰንብት

## አስደሳች ዜና ለቀንዲል ዲጂታል መፅሔት ተከታታዮች

የስነ ፅሁፍ ችሎታችሁን ከ 300 ሺህ ሰው በላይ በሚመለከተው መፅሔታችን ላይ ማውጣት ይፈልጋሉ??
እንገድያውስ ቀንዲል ዲጂታል መፅሔት በሚከተሉት አምዶች ፀሀፊዎችን ትፈልጋለች ::

#መዝናኛ
#ስነ-ልቦና
#ታሪክ
#ስፖርት
#ቴክኖሎጂ

በነዚህ አምዶች ፅሁፎችን በቋሚነት መፃፍና አምዳኛ መሆን የምትፈልጉ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የምታሟሉ

ፆታ -ወንድ/ሴት
ኢትዮጵያዊ
በበጎ ፍቃድ የሚሰራ
ከብሔርና ከየትኛውም የፖለቲካ አስተሳሰብ ነፃ የሆነ።

እስከ መጋቢት 30/2011 ድረስ በስልክ በመደወልና ፅሁፎቻችሁን በ ኢሜል በመላክ መወዳደር የምትችሉ መሆኑን በትህትና እንገልፃለን፡፡

✆0912178520
✆0920019699

#ቴክኖሎጂ

በያሬድ ለማ

## 3D Metal Printer



ከቅርብ ኣመታት ወዲህ ፕላስቲክ እና የተለያዩ ቁሶችን በተለያየ እና ውስብስብ በሆነ ቅርፅ የሚያትም ማሽን ሰርቶ ያሳየን ዘንድሮም የብረታብረት ቁሳቁሶችን በተለያዩ ቅርፃቅርፆች የሚቀይር ማተምያ እንካቹ ብሎናል::

ይህ ማሽን በአውሮፓውያኑ አቆጣጠር በ 2017 ማርክፎርጅድ በተባለ ድርጅት በ 100,000$ ለገበያ ቀርቦ የነበረ ቢሆንም የሚያትማቸው ቅርፆች ግን በመጠን ኣነስ ያሉ ነብሩ :: ባሳለፍነው የፈረንጆች ኣመት ደሞ በመጠን ትላልቅ የሚባሉ የብረታብረት ቅርፆችን እንዲያወጣ የተሻለ የኮምፒውተር መተግብሪያ ተሰርቶለት ለገበያ ቀርቡዋል::

ይህ የዘርፉን እንዲስትሪ በላቀ ደርጃ እንደሚያራምደው የታመነለት ማተምያ ማሽን በተለመደው ኣሰራር የማይደፈሩ ኣካላትን በቀላሉ እና በወጪ ቆጣቢ መንገድ እንደሚያትም ተነግሮለታል:: በተጨማሪም የብረታብረት ኢንድስትሪወችን ምርት በእጥፉ እንደሚጨምርም ይጠበቃል።

## ፖሊቴሊን(1954)




ዕለታዊ ህይወታችን ያለ ፖሊቴሊን ማሰብ ይከብዳል። ከፕላስቲክ የቁሳቁስ መያዣ እስከ ላውንደሪ ልባሶች- የዘይትና የውሃ መያዧዎች ድረስ የፓሊቴሊን ምርቶች በየቦታው የሚገኙና የሚታዩ ናቸው። በአሁኑ ወቅት በመላው ዓለም የፖሊቴሊን ኢንደስትሪ የ7 ቢሊዮን ዶላር ቢዝነስ ለመሆን በቅቷል። ይህ ጠቃሚ ቁስ የተገኘው በአጋጣሚ ሲሆን ዘመኑም እ.ኤ.አ 1953 ነበር። ጀርመናዊ ኬሚስት ካርል ዚግለር በዚያን ወቅት ኬሰር ዊሊኼለም በተሰኘው ኢንስቲትዩት በፉሪ ራዲካልስ ሞለኪውሎች ላይ ምርምር በሚያደርጉበት ወቅር ረስቶ በተወው የኬሚካል ውሁድ ላይ በታየ አዲስና ያልተለመደ የካርቦን አተሞች ሠንሠለት የተነሳ ፖሊቴሊንን ለማግኘት ችሏል።

ጊሊዮ ናታ የተሰኘ ጣሊያናዊ ኬሚስት በዚግለር ሥራ ላይ የራሱን ጥረት በማከል ፖሊቴሊን እውን ሊሆን የሚችልበትን መንገድ ፈጥሯል። ይህ ማቴሪያል ከምግብ መያዣዎች እስከ ለምንጣፍ ሥራ የሚያገለግል ፋይበር ድረስ ለመስራት አስችሏል። ናታ እና ዚግለር ለዚህ ፈጠራቸው እ.ኤ.አ በ1963 በጋራ በኬሚስትሪ የኖቤል ሽልማትን አግኝተዋል። ዛሬ ዓለም እነዚህ በቀላሉ ሟሙተውና በስብሰው የማይጠፉ የፕላስቲክ ምርቶች ያስጉኛል በማለት በቀላሉ በስብሰው የሚጠፉ ፕላስቲኮችን ለማምረት ጥረት እያደረገና ቴክኖሎጂውን ወደሌላ ከፍታ ከፍ ለማድረግ ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛሉ።

ሰላም!!



በዮናስ ሀ/ማርቆስ
( lijyoha@gmail.com)





# መልህቅ

በጥር 2010 ዓ.ም ለህትመት የበቃውና በዘነበ ወላ የተፃፈው መልህቅ የተሰኘውን መፅሀፍ እንድታነቡት ጋበዝኳችሁ።

"በአለማችን ላይ ከባድ የሚባለው ስራ ማዕድን ቁፋሮ ነው።በልዩ ልዩ ኬሚካል መበከል ጥልቅ ጉድጓድ ውስጥ እየሰሩ የሚያጋጥመው የአየር እጥረት ያም በዛ ብሎ በናዳ ምክንያት መሞት አለ።ሌላው የአለማችን ከባዱ ስራ መርከበኝነት ነው።

ከወዳጅ ዘመድ በአጠቃላይ ከሰው ዘር ለዘለአለሙ በሚመስል ሁኔታ ተቆራርጦ ባህር ላይ መቅዘፉ ከማዕበል ጋር መጋተሩ የራሱ አሳር አለው።

ይህ ሁሉ መከራ በፍጥረት የሚረሳው መርከቧ ፊቷን ወደ ወደብ የመለሰች ዕለት ነው።"(ከመፅሀፉ የተወሰደ)
በ 448 ገፆች የተሰናዳው "መልህቅ"ለሀገር ውስጥ በ150 ብር ለውጭ ሀገራት በ 25 የአሜሪካ ዶላር ለገበያ ቀርቧል።ደራሲው ከዚህ ቀደም:-
1:- "ህይወት በባህር ውስጥ"
2:-"ማስታወሻ"
3:- "ልጅነት" የተሰኙ ስራዎቹን ማድረሱ ይታወሳል።





# ደቦ

ይህ በዓይነቱም በይዘቱም ለየት ያለ መፅሀፍ ነው።ርዕሱ "ደቦ" ሲሰኝ 60 ደራሲያን ያካተተ ነው።በ ሰኔ ወር 2010ዓ.ም ነበር ለህትመት የበቃው ይህ መፅሀፍ በውስጡም

*ፍልስፍና
*ቃለመጠይቅ
*ህብረተሰብ
*ወጎች-ትዝታና ትውስታ
*ነገረ ድርሰት
*ታሪክ
*ፖለቲካ
*ህግ
*ፎክሎር(ባህል)
*የጉዞ ማስታወሻ
*ግጥሞች
*ትረካዎች
*ትርጉም አጫጭር ትረካዎች

የያዘ ሲሆን በዚህ መድብል የተካተቱ ስብስቦች የተፃፉበት ዘመን መቶ አመታትን ይሸፍናል።ማለትም ድርሰቶቹ ከ1910 እስከ 2010 ዓ.ም ድረስ ባሉ አመታት የተጻፉ ናቸው። ኅሩይ ወልደስላሴ(ብላቴን ጌታ) : ሸብሩ ተድላ(ፕሮፌሰር) : ዘነበ ወላ : ዳንኤል ክብረት : ሰረፀ ፍሬስብሀት : አለማየሁ ገላጋይ : ዮሀንስ አድማሱ : እንዲሁም ሌሎች እውቅና አዲስ ደራሲዎች ተሳትፈውበታል።የአርትኦት ስራውን እንዳለጌታ ከበደ ከውኖታል።መፅሀፉ በ 170ብር ለገበያ ቀርቧል።



# የተቆለፈበት ቁልፍ

በ ምህረት ደበበ(ዶ/ር)በመጋቢት ወር 2005 ዓ.ም ለንባብ የበቃውና ጥሩ ተቀባይነትን ያገኘ መፅሀፍ ነው።እስከ 2011 ድረስ ለ 15 ጊዜ ለህትመት በቅቷል። ምህረት ደበበ(ዶ/ር) በሙያው የአእምሮ ሀኪም ሲሆን በተጨማሪም በአስተሳሰብና የአእምሮ ለውጥ ዙሪያ ማሰብ:ማጥናትና ማስተማር ያዘወትራል።ህብረተሰባዊ ለውጥ ከግለሰቦች የአስተሳሰብ ለውጥ እንደሚጀምር ይናገራል።ይህ መፅሀፍም በዚሁ የለውጥ አሳብ ዙሪያ የሚያጠነጥን ትረካ ነው።በ432 ገፆች የተሰናዳውና ለሀገር ውስጥ በ180 ብር ለውጭ ሀገራት አንባብያን በ25 የአሜሪካ ዶላር ለገበያ ቀርቧል።

ethio Spark

ETHIO SPARK SOFTWARE DEVELOPMENT

Our Services

Software system development
Mobile application development for IPhone and Android
Desktop application development for Windows, Linux and Mac OS
Website development with an attractive user interface and better user experience

All of our developments are very affordable and customer based.
Our goal is your satisfaction in our work.

✆0975128309

ESQUARE
# ESQUARE ADVERTIZING

-Conferences
-Fundraising
-Anniversaries
-Birthday
-Graduation
-Festivals
-Magazines
-Graphics Designing
-promotion
-Exhibition
-Tornaments & Other Events

With MH graphics & Ermi Event Organizer

**For More Information Dial**

0912178520
0920019699

# ምስጋና

የሰው ልጅ ብዙ ያስባል እግዚአብሔር ግን መከናወንን ይሰጣል። ከሁሉ አስቀድመን በመፅሔታችን መከናወንን ለሰጠን በብዙ ላገዘን እና ለረዳን፡ ጥበቃውን፡ምህረቱንና ቸርነቱን ላበዛልን፡ ከኛ ላልተለየን በዚህች ቅፅፈት በበዛባት ዓለም  እኔ እና እናንተ ግን ዛሬ ላይ  በያለንበት ለመገኘታችን ፍቃዱ ለሆነው ሀያሉ እግዚአብሔር ምስጋና ይድረሰው።

ቀንዲል ዲጂታል መፅሔትን ስናዘጋጅ ሞራል የሰጡንን ያበረታቱንን አቶ ታሪኩ ግርማ ና የቅን-ድል ኢትዮጵያ አባላት  ምስጋናችን በያሉበት ይድረሳቸው። እንዲሁም መፅሔታችንን ይበልጥ ዲጂታላይዝ ለማድረግ በምናደርገው እንቅስቃሴ  ውድ ጊዜያቸውን እና እውቀታቸውን በነፃ ሰውተው የቀንዲል መፅሔት ሞባይል መተግበርያ ለሰሩልን የኢትዮ ስፓርክ ባለቤት ሄኖክ መንግስቱ ምስጋናችን የላቀ ነው።  እንዲሁም መፅሔታችንን በተወዳጅ የቴሌግራም ቻናላቸው ላይ የለቀቁልን TIKVAH - ETH፡ ግጥም ብቻ፡ዞዳይክና ከመፅሐፍት አለም ቻናሎች ምስገናችን ይድረሳቸው።

እናንተም ውድ አንባቢዎች የመጀመርያ ስራችንን ተመልክታች ለላካችሁልን ገንቢና መልካም  አስተያየት እጅግ አድርገን እያመሰገንን አሁንም አስተያየታችሁ አይለየን እንላለን።

ሰላማችሁ ይብዛ!!

ቀንዲል Digital Magazine

@KendilM

KendilM